ከፍተኛ ጥራት ያለው
የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት እቅድ

ሰኔ 2009


የትምህርት ጥራትና ፍትህ ክፍል

አድራሻ፤ 4700 South Yosemite
Greenwood Village, CO 80111

# ሂ ደ ት

ተኅሣሥ 2008፣ የድስትሪክት የ 'Title III' እንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም መርሀ/እቅድ፣ የድስትሪክት እንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም መርሀን ለሚከተሉት ግቦች ለመጀመር ተወያዩ፤

- ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አገልግሎት መስጠት በተመለከተ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች አጭርና ግልፅ መመሪያ መስጠት።
- እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በተመለከተ የነበሩትን የድስትሪክት ጥረቶች በአንድ ሰነድ/ፋይል ማቀናበር።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ልምድ/ተሞክሮ ለማሻሻል ከሌሎች ድስትሪክት ክፍሎች ጋር አብሮ መስራት።
- ለፌዴራል እና ለክፍለ ግዛት ህጎች መታዘዝ።

---

ቡድኑ የተደራጀው፣ ከድስትሪክት አስተዳደር፣ ከትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ከድስትሪክት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ ከጠቅላላ ትምህርት መምህራን፣ ከወላጆች፣ ከማህበረሰብና ከነጋዴ አባላት፣ እንደዚሁም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያዎች የተወጣጡ ተወካዮች አባላት ሲሆን፣ በ8 ትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ እያንዳንዱ ቡድን የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም/ትምህርት መርሀ ክፍል ላይ አተኮሩ። ለተከፋፈሉት ቡድኖች የተሰጠው ሥራ ጥናትና ምርምሩን፣ ህጋዊነቱን፣ 'Colorado Federal Integrated Review System (C-FIRS)' የሚባለውን የኮሎራዶና የፌዴራል የጋራ የክለሳ ሥርዓት ግኝቶችን፣ የድስትሪክት ዕሴቶችና ግቦች፣ መረጃ/ውሁብ እንደዚሁም የሕዝብ ብዛትና ሥነ ሕዝብ፣ በተጨማሪም ወቅታዊ ልምምዶችን መገምገምና ከሚመለከታቸው ግለሰቦች በኮምፒዩተር በታገዘ የዳሰሳ ጥናቶችና በቡድን ውይይት የድስትሪክት ግለሰቦች አስተያየቶችን ማግኘት ነው። በተጨማሪም፣ ከኮሚቴው ሥራ ጋር በተገናኘ መልኩ የራሳቸውን የተለያዩ አመለካከቶች የሚገልጹ ሃሳቦች እና ልምዶች ሰጥተዋል።

---

የመጨረሻው ውጤት አጭርና ግልጽ፣ እንደዚሁም መምህራንን፣ ወላጆችን እና አስተዳደሮችን እንዲያካትት የተደረገና **ለሁሉም የተዘጋጀ** ምቹ የሆነ ሰነድ ነው። ስለዚህም፣ እቅዱ በራሱ ስለ ሚዘና፣ መለያ፣ ስልጠናና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ ሚናን በተመለከተ ለሕግ መታዘዝ መስፈርቶችን የሚመለከቱ የተወሰኑ ዝርዝር ሀሳቦችን አያካትትም። እነዚያ የተወሰኑ ዝርዝር ሀሳቦች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎች መመሪያ ውስጥ ይገኛሉ፤ መመሪያዎቹም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያዎች በይፋ የተዘጋጁ ናቸው።

በ2009 ሴሜስቴር በሙሉ፣ ከእያንዳንዳቸው የተከፋፈሉት ከ8 ቡድኖች የተወጣጡ ተወካዮች የራሳቸውን የግል ክፍሎች ፈጠረው ያገኙትን መረጃዎች ለተከፋፈሉ አማካሪ ቡድኖች (የድስትሪክቱ የ 'Title III' አማካሪ ኮሚቴ) እንዲከለስና እንዲጠቃለል አቀረቡ። ሥራው የተካሄደው በአራት መደበኛ ትላልቅ የቡድን ስብሰባዎች ጊዜያትና በትናንሽ ቡድኖች የኮሚቴ ሥራ ጊዜያት ነበር። የመጀመሪያው ክፍል የተጠናቀቀው ሰኔ 10፣ 2009 ነበር።

ከድስትሪክት መርሆች ጋር በመሆን፣እንደዚሁም ከክፍለ ግዛት እና ከፌዴራል ሕጎች ጋር ለማመሳከርና አብሮ መሄዱን ለማረጋገጥ፣ እቅዱ ቢያንስ በየሦስት ዓመቱ ይገመገማል። (ሰኔ 10፣ 2009 የቅርብ ጊዜ ሠነድ ነው።)

ለዚህ መርሀ/እቅድ መዘጋጀት አስተዋጽኦ ላደረጉት ለሚከተሉት ሰዎች የላቀ ምስጋና እናቀርባለን፤



## የድስትሪክት አመራር
Elliott Asp፣ የክንዋኔ ማሻሻል ረዳት የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ
Tera Helmon፣ የበላይ አለቃr, ጥራትና ፍትሃዊነት
Eric Kophs፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ
Cynde Fischer፣ የመለስተኛ ትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ
Harry Bull፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ
Holly Porter፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ክፍል ኃላፊ

## የትምህርት ቤት አመራር
Stacey Peoples፣ ኃላፊ፣ Highline
Amanda Waleski ፣ ረዳት ኃላፊ፣ Eastridge
Linda Hezlep ፣ ኃላፊ፣ Peakview
Dee Bench፣ ኃላፊ፣ Indian Ridge
Joleta Gallozzi፣ ረዳት ኃላፊ፣ Fox Hollow
David Gonzales፣ ረዳት ኃላፊ፣ Prairie
Jeanette Patterson፣ ኃላፊ፣ Horizon
Floyd Cobb፣ ረዳት ኃላፊ፣ Cherry Creek
Rebecca Moehring፣ ረዳት ኃላፊ፣ Cherokee Trail

## የጠቅላላ ትምህርት መምህራን
Holly Reifman፣ 2ኛ ክፍል፣ Holly Ridge Primary
Mary Christensen-Cooper፣ ሒሳብ፣ Prairie
Carma Benitez፣ 5ኛ ክፍል፣ Village East
Katie Warnke፣ እንግሊዝኛ፣ Campus
Terese LeFavor፣ ሥነ ጥበብ፣ Cherokee Trail

## የድስትሪክት አቀናባሪዎችና አሰልጣኞች
Teresa Cummins፣የፌዴራል ፕሮግራሞች አቀናባሪ
La Toyua Tolbert፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራም አቀናባሪ
Lori Sayler፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራም አቀናባሪ
Julie Ignacz፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራም የለላቸው ትምህርት ቤቶች አቀናባሪ
Julie Sack፣ የ 'Title I' አቀናባሪ
Tanya Batzel፣የተለዩ ተማሪዎች ተቆጣጣሪ
Mark Overmeyer፣የድስትሪክት የማንበብና የመጻፍ ፕሮግራም አቀናባሪ
Sue Khair፣ የድስትሪክት የማንበብና የመጻፍ አቀናባሪ
Mary Dove፣ የጣልቃ ገብነት ምላሽ አቀናባሪ
Stephanie Boyd፣ የግምገማ/የሚዘና አቀናባሪ
Ann Zimmer፣ የቴክኖሎጂ አሰልጣኝ

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያዎች
Erin Davis፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Red Hawk Ridge
Dayna Perez፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Cherry Creek
Janis Angermayr፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Cimarron
Kathryn Dragseth፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Village East
Meg Lucero፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ/አሰልጣኝ Highline
Celina Campos፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Laredo
Julie Hofmann፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Overland
Maire Minnis-Turk፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Polton
Mark Hernandez፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Eastridge Heather Stevens፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Sagebrush
Michelle Carnes፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ፣ Thunder Ridge

## የድስትሪክት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች
Rachael Rosales፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም የአስተዳደሪ ጸሃፊ
Dave Roybal፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራም መረጃ ተንታኝ

## ወላጆች፣ የቋንቋና የባህል ድጋፍ ሰጪዎች እና የማኅበረሰብ አባላት
Pilar Lopez፣ ወላጅ
Juan Garcia, ፣ ወላጅ
Leah Lee፣ የኮሪያ ቋንቋና ባህል ድጋፍ ሰጪ
Anna McInroy፣ የሩሲያ ቋንቋና ባህል ድጋፍ ሰጪ
Miracle Choate፣ የእስፓኒሽ ቋንቋና ባህል ድጋፍ ሰጪ
Ivonne Tovar-Vargas፣ የእስፓኒሽ ቋንቋና ባህል ድጋፍ ሰጪ
Susan Lythgoe፣ ኃላፊ፣ የመማሪያ ምንጭ
Deborah Agar፣ የተለያዩ ቋንቋዎች ፕሮግራም አቀናባሪ፣ Regis University

# ማውጫ


ዓላማ......1

ኃላፊነት......2

ህጋዊ መስፈርቶች ......4

የህዝብ ብዛትና ስርጭት......10

እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን መለየት......12

እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን መገምገም ......14

እንደገና መመደብና ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራሙን ማጠናቀቅ ......17

ሥርዓተ ትምህርት......18

የማስተማሪያ ልምምዶችና ዘዴዎች......19

የተለያዩ የአገልግሎቶች ......21

ጣልቃ ገብነትና ድጋፍ መስጠት......22

ሙያዊ ዕድገት......24

የወላጆች ተሳትፎ......27

የፈላሾች እና የስደተኞች ቤተሰቦች......30

የቋንቋ ፍች እና ትርጉም......32

ግምገማ......33

የቃላት ዝርዝርና ፍች......35

Appendix A – የቤት ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት......40

Appendix B – ማስረጃ......41

**የድስትሪክታችን ተልዕኮ፤**

*"እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስብ፣ እንዲማር፣ እንዲከናወንለትና ለሌላው ደንታ እንዲኖረው/እንዲኖራት መቀስቀስ ነው።"*

***ጥራት ማለት ፍትሃዊነት ለሁሉም ማለት ነው***

ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የወጣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት አጠቃላይ መርህ/እቅድ እያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ፣ ቤተሰብ፣ የማኅበረሰብ አባል እና ሁሉም የትምህርት ባለሙያዎች እንዲያስቡ፣ እንዲማሩ፣ እንዲከናወንላቸውና ለሌሎች ደንታ ያላቸው እንዲሆኑ ለማነሳሳት ነው።

| | |
|---|---|
| ***እያንዳንዱ ተማሪ*** | ▪ በቼሪ ክሪክ ውስጥ የላቀ ሥራን በፍትሃዊነት መሥራት ዋናውና የሚናተኩርበት ተግባራችን ነው። የሁሉንም ተማሪዎች ክንውን ለመጨመርና በተማሪዎች ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ የትምህርት ውጤታቸውን መተንበይን ለማስቀረት በትጋት እንሰራለን።<br>▪ የማኅበረሰባችንን ስብጥር የሚያንጸባርቁና ብቃት ያላቸው፣ እውቀት የተሞላቸው፣ እና ለወጣቶች በጣም ደንታ ያላቸውን ሰራተኞች መሳብ አስፈላጊ ነው። |
| ***እንዲያስብ*** | ▪ የጥብቅ ትርጉም ከአስፈላጊ መመዘኛዎች አንጻር ሲወሰን ድስትሪክቱ አስተማማኛና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሥርዓተ-ትምህርትን ይደግፋል። ትርጉሙ የተማሪ ሥራን በተመለከተ የጋራ ሚዘናዎችንና ምሳሌዎችን ያካትታል፣ እንደዚሁም በድስትሪክቱ በሞላ ትምህርትንና የተማሪ ክንዋኔን በተመለከተ በወል/በጋራ የሚጠበቁትን ጉዳዮች ያካትታል።<br>▪ ተማሪዎች "አዕምሮአቸውን መጠቀም" እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ ማስተማር፣ ይህም ማለት ተማሪዎች ስልታዊ አስተሳሰብ፣ ማስተዋል፣ ትጋት/ጽናት፣ የፈጠራ ችሎታ፣ እና የተለያዩ አሠራሮችን የሚጠይቁ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሥራቸውን ማከናወን እንዲችሉ መርዳት ማለት ነው። ብልሃተኛ የሆኑ የሰው ልጆች መሰረታዊ መገለጫ መረጃን መያዝ ብቻ ሳይሆን፣ መረጃውን እንደተ እንደሚጠቀሙ ጭምርም ማወቅ ነው። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች በግልጽና በትክክል ማሰብና ከሰዎች ጋር መግባባት ማወቅ፣ ያለፉትን ልምዶች/ተሞክሮዎች በአዳዲስ ሁኔታዎች ውስጥ መጠቀም እና ባለማቋረጥ ለመማር ፈቃደኛ መሆንን ማወቅ አለባቸው። |
| ***እንዲማር*** | ▪ በድስትሪክታችን ውስጥ፣ ሁሉም መምህራን የአሁኖችንና የወደፊት ተማሪዎችን ለማስተማር እውቀቱንና ችሎታዎቹን ሊኖራቸው ይገባል።<br>▪ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ተማሪዎችን፣ ወላጆችን እና የማኅበረሰብ አባላትን በትምህርት ሂደት ውስጥ ያሳትፋል። |
| ***እንዲከናወንለት*** | ▪ ተማሪዎቻችን ስብጥርነት ያላቸውና ወጣቶች የሆነ እና በክፍለ ግዛት እና በሀገር አቀፍ 'CSAP, ACT and SAT ' በሚባሉ ፈተናዎች ከአማካይ በላይ ነጥብ የሚያመጡ ናቸው። ገደብ የለለው እውቀት ያላቸውና የወደፊት ተስፋ ያላቸው ናቸው።<br>▪ በቼሪ ክሪክ ውስጥ፣ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው በኃላ የሚፈልጉት ማንኛውም ዓይነት እቅድ ቢኖራቸውም፣ በከፍተኛ ትምህርት እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስፈልጋቸውን እውቀትና ችሎታዎች ሊኖራቸው እንደሚገባ እናምናለን። በዚህ ዘመን፣ ተማሪዎች ኮሌጅ ለመግባት፣ የውትድርና አገልግሎት ውስጥ ለመግባት፣ ወይም በቀጥታ ሥራ ለመጀመርም ቢያቅዱም ሆነ ባያቅዱ፣ ተማሪዎች ተመሳሳይ እውቀትና ችሎታዎች እንደሚፈልጉ እናውቃለን።<br>▪ 'Blue Ribbon and John Irwin School of Excellence' የሚባሉትን በትምህርት ጥራት ሥያሜ የሚሰጡትን ሽልማቶች ጨምሮ፣ ትምህርት ቤቶቻችን ከፍተኛ አክብሮቶችን አግኝቷል፣ የትምህርት ቤቶቻችን ሁለት-ሦስተኛ 'እጅግ በጣም ጥሩ' ደረጃ ያላቸው ወይም በኮሎራዶ የትምህርት ቢሮ 'ከፍተኛ' ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ፣ 'ዝቅተኛ ደረጃ' ወይም 'በቂ ያልሆነ' ደረጃ ያለው ትምህርት ቤት የለም። |
| ***ለሌላው ደንታ ያለው እንዲሆን/እን ዲትሆን*** | ▪ ከድስትሪክት ግቦች ውስጥ አንዱ በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ለመሳተፍ ዝግጁ የሆኑና በተለያዩ የዜጎች/የህዝብ ጉዳዮች/ተግባራት ውስጥ ለመሳተፍ የሚያልሙትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመራቂ ተማሪዎች ፐርሰንት መጨመር ነው። ለምሳሌ፣ የመንግሥት የአሰራር ሂደት፣ ምርጫ፣ የነጻ አገልግሎት መስጠትና ሌሎች የማኅበረሰብ አገልግሎት ዓይነቶችን አስመልክቶ ተማሪዎች እውቀት ቢኖራቸው አስፈላጊ ነው።<br>▪ በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች አዎንታዊ ባህሪይ ያላቸውና ልጆችና ወጣቶች እንዲሻሻሉ፣ ጠንካራ ሕዝብ እንዲሆኑ፣ በህይወታቸው ውስጥ የተሻለ ምርጫ ማድረጉ እንዲችሉና በዕለታዊ ህይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በተሳካ ሁኔታ መቋቋም እንዲችሉ የሚረዱ 40 የእድገት እሴቶችን ሥራ ላይ አውለናል።<br>▪ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት በትምህርት ቤቶቻቸው ጨዋ የሆኑና ታማኝ፣ ሌሎችን ሰዎች የሚያከብሩ፣ እና የተለያዩ ባህሎችንና ሰዎችን የሚረዱና የሚቀበሉ ጥሩ ባህሪይና ሥነ-ምግባር ያላቸው የተማሪዎች ፐርሴንተጅ መጨመር ይፈልጋል። |
| ***ለመቀስቀስ ነው*** | **እንደ ቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ትልቅ ተልዕኮ ያለው የትምህርት ድርጅት/ተቋም የለም።** ሰራተኞቻችን እያንዳንዱን ልጅ በየቀኑ እንዲቀሰቅሱ እንጠይቃለን። ተማሪዎች ውስብስብና ተለዋዋጭ የሆነውን የዓለም ተግዳሮት እንዲቋቋሙ ለማዘጋጀ፣ ሥራችን ተማሪዎች የመማር ጉጉት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። |

*"አስተዋይነታችን ያለፈውን ነገር በማስታወሳችን ሳይሆን ፣ ለወደፊታችን ሃላፊነትን በመውሰዳችን ነው።"*
*~ጆርጅ በርናርድ ሻው*

በዚህ ጥረት ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች የሚያተኩሩ እሴቶች አሉን:

- ከሁሉም በፊት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ሰላምና ደኅንነት ማስቀደም፣
- ለመማር ምቹ የሆኑ እና ደህንነታቸው የተጠበቁና ለተማሪዎች ደንታ ያላቸው የመማሪያ ቦታዎችን መፍጠር፣
- ለእያንዳንዱ ተማሪ እድገትና ክንውን ከፍተኛ ተስፋ ማድረግ፣
- ከተማሪዎችና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት መፍጠርና ማዳበር፣
- የሚናገለግላቸውን ተማሪዎችና ቤተሰቦች ስብጥርነት መረዳትና ማክበር፣
- ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችንና የማኅበረሰብ አባላትን እንደ አባሪ/ሽሪክ በትምህርት ሂደት ውስጥ ማሳተፍ፣
- ተሳትፎንና አቅምን የሚገነቡና የሚያበረታቱ ተቋማዊ ስልቶችን መጠቀም፣
- የማኅበረሰባችንን ስብጥርነት የሚያንጸባርቁ፣ በቂ እውቀት ያላቸውና ለልጆች በጣም ደንታ ያላቸው ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች መቅጠር፣
- ለተማሪዎችና ለወላጆች ጽኑ የሆነ አገልግሎት መስጠት፣
- ራእይን ለማሳካት የሚደረጉትን የፈጠራ ችሎታዎችንና አዳዲስ ግኝቶችን ማበረታት፣
- ተቋሙን በቀጣይነት ማሻሻል፣
- የዕድሜ ልክ መማርን፣ የክንውንን፣ እና ሌሎችን የማገልገል ፍላጎትን ማበረታት ናቸው።

---

**የድስትሪክት ሰራተኞች**
ሁሉም የድስትሪክት ሰራተኞች ይህንን እቅድ በታማኝነት ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት አላባቸው። በየደርጃው ያሉት የተቋሙ ሰራተኞች በዚህ እቅድ ውስጥ የተነደፉትን ተግባራት የሚመለከቱ አዳዲስ ሥነ-ምግባራትንና አመለካከቶችን የመቅሰምና የማከናውን ኃላፊነት አለባቸው። ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤትና የትምህርት ድስትሪክት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ስኬት እንደ የድስትሪክት ኃላፊነት አድርጎ መቀበል አስፈላጊ ነው።

**የድስትሪክት አመራር**
በፌዴራል፣ በክፍለ ግዛትና በትምህርት ቦርድ በሚጠበቁ ጉዳዮች ላይ በመመስረት በየትምህርት ጥራት የተግባር ስልታዊ እቅድ ውስጥ የተነደፉትን የተቋሙን አጠቃላይ ግብ፣ ራዕይና ተልዕኮን ለማሳካት የድስትሪክት አመራርና የአስተዳደር ሰራተኞች የአመራርና የአስተዳደራዊ ሥራቸውንና ድጋፋቸውን ይቀጥሉበታል።

**የትምህርት ቤት አመራር**
የትምህርት ቤት አስተዳደርና አመራር የሚከሰቱትን ችግሮች ይቀርፋሉ፣ አስፈላጊውን ድጋፍን ይሰጣሉ፣ በተጨማሪም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ክንውንና ለዚህ እቅድ መተግበር ኃላፊነታቸውን በመንደፍ የሁሉንም አስተማሪዎች እድገት ያሻሽላሉ።

**አስተማሪዎችና የትምህርት ቤት ሰራተኞች**
በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በተደገፈ የማስተማሪያ አብነት/ሞዴል ውስጥ እንደተነደፈውና በዚህ እቅድ ውስጥ በተገለጹት ተግባራት መሰረት፣ ሁሉም ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ እንዲችሉ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ስምረት/ስኬታማነት ለማሳደግ፣ እያንዳንዱ አስተማሪ ተማሪዎችን የሚረዳ የማስተማር ልምድንና የተለያዩ ሚዘናዎችን የመጠቀም ችሎታ ሊኖረው/ሊኖራት ይገባል። እንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰምን በተመለከተ ባለሙያዎቹ ለይዘት ዙሪያ አስተማሪዎች ውጤታማ የማስተማሪያ ስልቶችን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣሉ።

**የመረጃዎች/የውሁቦች ትንተና**
ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ የሚገኝ መረጃ እንደ የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፍትሃዊ ግብ እቅድ አካል ይተነተናል። ትምህርት ቤቶች እንዲከልሱ የሚዘናዎችና የግምገማዎች ቢሮ ለኮሎራዶ እንግሊዚኛ ቋንቋ ሚዘናዎችና ለሌሎች ትርጉም ያላቸው ውሁቦች/መረጃዎች በየጊዜው ይሰጣቸዋል። ውጤቶቹን መተንተን በተመለከተ የድስትሪክት አመራር ለትምህርት ቤት አመራር አስፈላጊውን ድጋፍን ይሰጣል። ሂደታዊ የቋንቋ መቅሰም ውጤቶች፣ ሁለቱም መደበኛና አጠቃላይ፣ በአስተማሪዎችና በትምህርት ቤት አመራሮች በጋራ ትብብርነት ይቆጣጠራሉ።

**የወላጅ ሽሪክነት**
የወላጅ ሽሪክነት የሚካሄደው በዚህ እቅድ ውስጥ፣ በየወላጅ ተሳትፎ ክፍል ውስጥ በተነደፈው ውጤታማ በሆነ አሰራር መሰረት ነው። ወላጆችና ቤተሰቦች ተማሪዎችን ትርጉም ባላቸው ተሳትፎዎችና ሥራዎች ይደግፏቸዋል።

**ሙያዊ እድገት**
ሥራን መሰረት ያደረገ ተከታታይ ሙያዊ እድገት፣ የሙያዊ ሥልጠና የማኅበረሰብ ትብብር፣ በድስትሪክት የመማር ማስተማር አሰልጣኞች በኩል የአቻ-ለአቻ ሥልጠና ፣ እና ኃላፊዎች፣ ይህ እቅድ መተግበሩን የሚያረጋግጡበት ዘዴዎችን ያቀርባሉ።



# ህጋዊ መስፈርቶች

*"ትምህርት ትልቅ የለውጥ ኃይል ያለው የሰው ልጅ መብት ነው።"*

*~ኮፊ አናን ፣ የ2001 የኖበል የሰላም ሽልማት ተቀባይ*

## *ሪዕስ III*

ማንኛውም ተማሪ በትምህርቱ ወደ ኃላ እንዳይቀር የሚል አዋጅ፣ እንግሊዝኛው 'No Child Left Behind (NCLB)' የሚል፣ ሪዕስ III አዋጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋውን ብቃትና የትምህርቱን ይዘት እንዲጨብጡ የመደገፊያ ድጎማ ይሰጣል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንግሊዝኛንና የመደበኛ ትምህርታቸውን በተመለከተ ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት አለባቸው። አንዲ(ት)ም ተማሪ በትምህርቱ/ቷ ወደ ኃላ እንዳይቀር/እንዳትቀር የሚመለከት አዋጅ የትምህርት ፕሮግራምን መምረጥ በተመለከተ ባያጠብቅም፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋና በመደበኛ ትምህርታቸው መሻሻል እንዲያሳዩ ትልቅ ሃላፊነት ይፈለጋል። በሬዕስ III ሥር፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት መመዘኛዎችን ማውጣትና እነዚህን መመዘኛዎች ከክፍለ ግዛት የትምህርት ይዘት መመዘኛዎች ጋር እንዲያገናኙ ከክፍለ ግዛቶች ይፈለጋል። ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከክፍለ ግዛት የተሰጣቸው የሃላፊነት ሥርዓት ክፍል መሆናቸውንና በትምህርታቸው የሚያሳዩት መሻሻል በየጊዜው ቁጥጥር እንደሚደረግበት ማወቅ አለባቸው።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በተመለከተ አንዲ(ት)ም ልጅ በትምህርቱ/ቷ ወደ ኃላ እንዳይቀር/እንዳትቀር የሚመለከት አዋጅ የተወሰኑ ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፤

**የመመዘኛ ፈተና**

- የሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት በየዓመቱ በኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሚዘና ፈተና ይረጋገጣል።
- ሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ተሰጥኦና ሒሳብን በተመለከተ የክፍለ ግዛት የትምህርት ክንውን ፈተናዎችን ይወስዳሉ፤ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከአንድ ዓመት በታች የቆዩ ተማሪዎች የቋንቋ ተሰጥኦ የመመዘኛ ፈተናን ለዚያ መጀመሪያ ዓመት መውሰድ የለባቸውም።
- ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት በዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የቆዩና በሪዕስ III በሚደገፍ ፕሮግራም የተሳተፉ ተማሪዎች የምንባብና የቋንቋ ተሰጥኦ ፈተና በእንግሊዝኛ መውሰድ አለባቸው።

---

**ወላጆችን ማሳወቅ**

- ልጆችን በልዩ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም መመደብ ለምን እንዳስፈለገ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለወላጆች ያሳውቃል።
- በተጨማሪም፣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ወላጆችን በተለያዩ መንገዶች በመድረስ የልጆቻቸውን የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎ እንዲያውቁና እነርሱም በፕሮግራሙ በንቃት እንዲሳተፉ የተለያዩ ተግባራትን ይፈጽማል። ለበለጠ መረጃ የወላጆች ተሳትፎ ክፍልን ይመልከቱ።

### *ኃላፊነት*

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት 'Title III' የሚባለውን እርዳታ ይወስዳል፤ ስለዚህም፣ በግልጽ የሚመዘን ዓመታዊ የክንውን ግብ ላይ የመድረስ ኃላፊነት አለብን። ግቦቹ የሚጠቅሙት የቋንቋ ማስተማር ፕሮግራሞች ውጤታማነትን ለመመዘን ነው። ግቦቹ ሦስት አቢይ ዓላማዎች አሉት፤

- እንግሊዝኛ ቋንቋን መማር በተመለከተ ዓመታዊ መሻሻል ያሳዩ ተማሪዎች በፐርሰንት/በመቶኛ፣
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታን በተመለከተ አስፈላጊው የብቃት ደረጃ ላይ የደረሱ ተማሪዎች በፐርሰንት/በመቶኛ፣
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በተመለከተ ተገቢው ዓመታዊ መሻሻል መስፈርት ማሟላት ናቸው።

---

### *ፕሮግራም*

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት፤

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸው ውስን የሆኑትን ልጆች የሚያስተምሩ የቋንቋ ትምህርት መምህራን በቋንቋው የመጻፍና የመናገር የብቃት ደረጃቸው የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል።
- ፕሮግራሞቹ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍና እንግሊዝኛ ቋንቋ ግንዛቤ እንዳካተተ ያረጋግጣል ፣ እንደዚሁም ተማሪዎች የክፍል ግዛት የትምህርት ይዘት መመዘኛዎችን እንዲያሟሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸው ውስን የሆኑትን ልጆች ለማስተማር እቅዳችን ሳይንሳዊ በሆኑ የጥናትና ምርምር ላይ ይመሰረታል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን እቅድ ለማዘጋጀት ከአስተማሪዎች፣ ከጥናትና ምርምር አድራጊ ቡድኖች፣ ከትምህርት ቤት አስተዳደሮችና ከወላጆች ጋር፣ እንደዚሁም፣ ተገቢ ከሆነ፣ ትምህርት-ነክ ከሆኑ የከፍተኛ ትምህርት የማህበረሰብ ቡድኖችና ትርፋማ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር ምክክር አድርጓል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸው ውስን የሆኑት ልጆች ትምህርት በተመለከተ፣ ማንኛውንም የክፍለ ግዛት ህግ፣ የክፍለ ግዛት የህገ መንግሥታዊ ህግን ጨምሮ፣ ሳይጥስ ከ 3116(d)(5) ክፍል ጋር በሚዛመድ መልኩ ይፈጽማል።





## የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት አዋጅ

*(የሴኔት አዋጅ 462-1981፤ የሪዕስ 22 አንቀጽ 24፣ የተሻሻለ የኮሎራዶ የተሻሻለ ህግ)*

**ህጋዊ መግለጫ**

የጠቅላላ ጉባዔው በዚህ ክፍለ ግዛት ውስጥ የብዙ ተማሪዎች መግባቢያ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ በመሆኑ የትምህርት ችሎታቸው በጣም የተገደበ መሆኑን ይለያል፣ ይወስናል፣ እንደዚሁም ይገልጻል። የጠቅላላ ጉባዔው የተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎች ለማሻሻል የሽግግር ፕሮግራሞች እንደሚያስፍልጉ ይገነዘባል። በህዝብ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ብቃት ፕሮግራም ማውጣትና የነዚህን ፕሮግራሞች ወጪ ለመሸፈን ለተወሰኑ የትምህርት ድስትሪክቶች ገንዘብ ማካፋፈል የዚህ አንቀጽ ዓላማ ነው።

*(ክፍል 22-24-105 የድስትሪክት ሥልጣንና ተግባራትን እንደሚከተለው ይገልጻል)*

የሚከተሉት ተግባራት የድስትሪክቱ የሥራ ድርሻ ናቸው፤

- በወላጆች፣ በአስተማሪዎች፣ ወይም በሌሎች ሰዎች አስተውሎት/ምልከታና አስተያየት አማካይነት ዋና ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ያልሆነ ተማሪዎችን መለየት፣
- በትምህርት ክፍሉ በጸደቁ የተማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መመዘኛ ፈተናዎችንና ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ዋና ቋንቋቸው እንግሊዝኛ አለመሆኑን ለመወሰን ለተማሪዎቹ የማጣሪያ ፈተናን መስጠት፣
- በድስትሪክቱ ውስጥ ዋና ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ያልሆኑትን ተማሪዎች ለትምህርት ክፍሉ ማረጋገጥ፣
- ዋና ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ላልሆነ ተማሪዎች ፕሮግራሞችን ማውጣትና መስጠት ናቸው።

ዋና ቋንቋው/ዋ እንግሊዝኛ ያልሆነ ተማሪ በቂ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ግንዛቤ ስለለው/ስለሌላት ወይም በቋንቋው የመናገር ችሎታው/ዋ አናሳ ስለሆነ የትምህርት ክንውኑ/ኗ የተገደበ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪ ይባላል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ የችሎታ ብቃት በተማሪው/ዋ የትምህርት ድስትሪክት በሚሰጡ የተማሪ የቋንቋ መመዘኛ ፈተናዎች ይወሰናል። እንደዚህ ያለ ተማሪ ከሚከተሉት አንድ ወይም ከዚያም በላይ መገለጫዎች ይኖረዋል/ይኖራታል፤ ስለዚህም ተማሪው/ዋ እንደሚከተለው ይገለጻል/ትገለጻለች፤

- ሌላ ቋንቋ የሚ(ት)ናገር፣ እንግሊዝኛ ቋንቋን የማይረዳ ወይም የማይናገር ተማሪ
  ወይም
- እንግሊዝኛ ቋንቋን በተወሰነ ደረጃ የሚ(ት)ረዳ ወይም የሚ(ት)ናገር፣ ነገር ግን በዋነኛነት የም(ት)ረዳው ወይም የሚ(ት)ናገረው ሌላ ቋንቋ የሆነ ተማሪ
  ወይም
- እንግሊዝኛንና ሌላ(ሎች) አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋን የሚ(ት)ገነዘብ ወይም የሚ(ት)ናገር ሆኖ፣ ዋና ቋንቋው/ዋን ለመወሰን የሚያስቸግር ተማሪ፤ ይህም የሚሆነው የተማሪው/ዋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገትና ግንዛቤ፤

  1. የድስትሪክት ወይም የሀገር አቀፍ መደበኛ መመዘኛ ፈተናን የሚያሟላ/የሚታሟላ ወይም ከዚያ በታች የሆነ/ች
     ወይም
  2. በትምህርት ክፍሉ ከጸደቀው የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ መመዘኛ ፈተና ያላሟላ(ች) ተማሪ ከሆነ ነው።

# ድስትሪክቶች ውሰን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን የመደገፍ ኃላፊነትን እንዳለባቸው የሚመለከት የፌዴራል ህግ

የድስትሪክት ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች የመርዳት ኃላፊነት የሚመለከት የአሁኑ የዜጎች መብቶች ፖሊሲ ቢሮ በሚከተሉት የፌዴራል ህጎችና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ ይሞረኮዛል፤

| | |
|---|---|
| 1964 | 'Title VI' የሚባል የዜጎች መብቶች አዋጅ |
| 1968 | የመንታ ቋንቋ ትምህርት አዋጅ |
| 1970 | የግንቦት 25ኛ ማስታወሻ |
| 1974 | የ 'Lau'ና የ 'Nichols' የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ |
| 1974 | እኩል ትምህርት ዕድሎች አዋጅ |
| 1978 | የትምህርት መሻሻሎች |
| 1981 | የ 'Casteneda'ና 'Pickard' 5ኛ ውሳኔ |
| 1985 | 'OCR: Title VI' የሚባል የአናሳ ቋንቋ ሂደት |
| 1991 | አዲስ የተሻሻለ 'OCR' የሚባል ፖሊሲ |

**1964 'Title VI' የሚባል የዜጎች መብቶች አዋጅ**

በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በብሔር ላይ የተመሰረተ አድልዎን ይከለክላል። ድስትሪክቶች ለአናሳ ቋንቋ ተማሪዎች እኩል የትምህርት ዕድል መስጠት አለባቸው። ይህም ዕድል የሚረባቸውና ትርጉም ያለው መሆን አለበት። ይህም ለአማራጭ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም የቀረበ ነው። ትምህርት ቤቶች ሌሎች የሚያገኙትን ዕድሎች የተወሰኑ የግለሰቦችን ላይነፍጉ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች አገልግሎቶችን፣ የገንዘብ እርዳታን፣ ወይም ሌሎች ልዩ የሆኑ ወይም በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡትን ጥቅማጥቅሞች ላይሰጡ ይችላሉ።

**1968 የመንታ ቋንቋ አዋጅ**

የመንታ ቋንቋ አዋጅ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ልዩ የትምህርት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የሚመለከት የመጀመሪያ የፌዴራል ትኩረት ያገኘ ነው። እኩል የትምህርት ዕድል መስጠት ከተፈለገ፣ የመንታ ቋንቋ ፕሮግራሞች በፌዴራል መደገፍ አለባቸው።

## 1970 የግንቦት 25ኛ ማስታወሻ

የ 1964 ሪዕስ VI የዜጎች መብቶች አዋጅ ገለጻ። ግንቦት 25፣ 1970፣ የጤና ጥበቃ፣ የትምህርት፣ እና የበጎ አድራጎት ክፍሎች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር ችሎታ ያላቸው ልጆች ትምህርት በተመለከተ የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ስምምነቱ የትምህርት ድስትሪክቶች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ መጽሃፍትን መስጠትና ተመሳሳይ አስተማሪን ከመመደብ ባሻገር ልዩ ትኩረት እንዲሰጧቸው ያሳስባል። አንድ ዓይነት ትምህርት እኩል ትምህርት አይደለም። ተማሪዎቹ እንግሊዝኛን ባለማወቃቸው የተነሳ፣ የአይምሮ ችግር ያለባቸው መማሪያ ክፍል ውስጥ መመደብ፣ ለኮሌጅ ትምህርት መዘጋጃ ኮርሶችን መከለከል፣ ወይም በሌላ ዓይነት መልኩ መታየት የለባቸውም። በመጨረሻም፣ የትምህርት ድስትሪክቶች የትምህርት ተግባራትን ለወላጆች በሚገባቸው ቋንቋ የማሳወቅና ከሌሎች የመግባቢያ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ከሆነ ወላጆች ጋር በእኩልነት እንዲረዱና እኩል ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ የመደገፍ ኃላፊነት አለባቸው። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቹ የቋንቋን ችግር እንዲቀርፉ የመርዳትና በትምህርታቸው በደንብ እንዲሳተፉ የተለያዩ ዕድሎችን የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

የአማራጭ ፕሮግራም አስፈላጊነት ጥያቄ የሚቀረው የአናሳ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ በሆነ ሁኔታ በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ መቻላቸውን በማረጋገጥ ነው። ይህ ካልሆነ፣ የትምህርት ድስትሪክት አማራጭ የቋንቋ ፕሮግራም መስጠት አለበት። ዲስትሪክቶች ፕሮግራሙ የአናሳ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማገዝ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ጥሩና ተገቢ ፕሮግራሞች መኖራቸውን ለማረጋገጥ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። ፕሮግራሙ

# ህጋዊ መስፈርቶች

የሚመለከታቸውን ተማሪዎች በተመለከተ አፈጻጸሙንና ሂደቱን አስመልክቶ ጥሩና ተገቢ ፕሮግራም ትክክልና ሙሉ መረጃ ማካተት አለበት። ተማሪዎች የማስተማሪያ ቋንቋን መናገር ባለመቻላቸውና ቋንቋውን ባለመገንዘባቸው የተነሳ ንቁና ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ ከማድረግ መገለል የለባቸውም።

**1974** **የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ 'Lau' እና የ 'Nichols' ንጽጽር**

በ 1974፣ በሰን ፍራንሲስኮ የትምህርት ድስትሪክት 1800 የቻይና ተማሪዎች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስላላቸው ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እኩል ትምህርት እየተሰጣቸው አይደለም የሚል ክስ በተማሪ ወላጆች ቀርቦ፣ ይህ የ 'Lau' እና የ 'Nichols' ንጽጽር የክስ ጉዳይ በተመለከተ የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለወላጆቹ/ለተማሪዎቹ ፈርዶላቸዋል። ዳኛው ዊልያም ኦ ዶግላስ ይህንን ያጸደቀበት ምክንያት ተማሪዎቹ የተወሰነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስለነበራቸው፣ ወይም ቋንቋውን በጭራሽ ባለመቻላቸው የተነሳ ትርጉም ካለው ትምህርት ስለተገለሉ ነው። የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ አስተማሪን መመደብና ተመሳሳይ የመማሪያ መጽሃፍትን ማቅረብ በቂ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን የአናሳ ቋንቋና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ትምህርቱ ትርጉም ያለው እንዲሆንላቸው ለተማሪዎቹ ልዩ ድጋፍ መሰጠት እንደነበረበት ወስኗል። ፍርድ ቤቱ የ 'Lau' እቅድን 20 ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ የታወቁ የአናሳ ቋንቋ ተማሪዎች ላላቸው የትምህርት ድስትሪክቶች እንዲፈጸም አስገደደ። በትምህርት ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን እኩል ተሳትፎ የሚገድብ ማንኛውንም ጉዳይ ለመቅረፍ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

**1978** **የትምህርት መሻሻሎች**

የ 1978 የትምህርት መሻሻሎች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ችሎታ ላላቸውና ውስን የቋንቋው ብቃት ላላቸው ተማሪዎች የመንታ ፕሮግራሞች መስፈርት የማሟላት ዕድልን አሰፍቷል። ይህ ጉዳይ የሚመለከተው የእንግሊዝኛ ቋንቋን መናገር የማይችሉ፣ ቋንቋውን የማይረዱ፣ በቋንቋው ማንበብ፣ ወይም መጻፍ የማይችሉ ተማሪዎችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተሳካ ሁኔታ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳይማሩ መከለከል ነው ('Public Law' 95-561)።

**1981** **የ 'Casteneda' እና የ 'Pickard' 5ኛ የውሳኔ ንጽጽር**

ይህ በረይመንድቪል፣ ተክሰስ (Raymondville, Texas) የተደረገው ውሳኔ ትምህርት ቤቶች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ፕሮግራሞች ሊኖሯቸው እንድሚገባና ፕሮግራሞቹም በህግ ላይ መመስረት እንዳለባቸው ይገልጻል። ፕሮግራሙም መውጣት ብቻ ሳይሆን መፈጸም አለበት። እንደዚሁም፣ የፕሮግራሙ ሥራ ላይ መዋልና አፈጻጸም ይገመገማል።

**1991** **የዜጎች መብቶች ቢሮ ፖሊሲ፤ ሦስት ረዣዥም የካስታንዳ አካሄድ**

**የትምህርት አካሄድ አስፈላጊነት**

የእያንዳንዱን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ፍላጎት ለማሟላት የተወሰነ የትምህርት አሰጣጥ መምረጥ የእያንዳንዱ የትምህርት ድስትሪክት መብት ነው። የትምህርት ድስትሪክት በተወሰኑ ባለሙያዎች የተረጋገጡትን፣ ወይም እንደ ህጋዊ የትምህርት አሰጣጥ ስልት የታወቁትን ማንኛውንም የትምህርት አሰጣጥ ስልት መጠቀም ይችላል።

# ህጋዊ መስፈርቶች

በድስትሪክቱ የተመረጠ የትምህርት አሰጣጥ እንዳለ ሆኖ፣ ከሪዕስ VI አንጻር ሲታይ ህጋዊነቱ በሁለት መልኩ ይታያል፤(1) የትምህርት አሰጣጡ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ መሻሻል መጥቀም፣ እና (2) በድስትሪክት የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የትምህርት አሰጣጡ ትርጉም ያለውና ውጤታማ የሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተሳትፎን የሚያመጣ መሆኑ ናቸው። የዜጎች መብቶች ቢሮ ዲስትሪክቶች የራሳቸውን የተለዩ የፕሮግራም ግቦች እንዲያዘጋጁ ያበረታታል። እንደዚህ ያሉ ግቦች በመደበኛነት ቢዘጋጁም ሆነ ባይዘጋጁ፣ የዜጎች መብቶች ቢሮ ፕሮግራሙ ከላይ የተሰጡትን የሪዕስ VI ሁለት መስፈርቶች እንዲያሟላ ይጠበቃል።

**አግባብ ያለው አፈጻጸም፤ የሰራተኞች መስፈርት፣ ከፕሮግራሙ መውጫያ መስፈርትና፣ ልዩ ችሎታ/ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችና የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን ማግኘት**

ድስትሪክት የትምህርት አሰጣጥ ሂደትን ከወሰነ በኃላ፣ ፕሮግራሙን ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊውን ነገርና ድጋፍ ይፈልጋል። በድስትሪክቶች የሚካሄዱት የትምህርት አሰጣጥ ሂደቶች ልዩነት፣ በድስትሪክቶቹ ውስጥ እንደሚገለገሉት ማህበረሰቦች ልዩነት ነው።

**የፕሮግራም ግምገማ**

ድስትሪክት የትምህርት አሰጣጥ ሂደትን ከወሰነ በኃላ፣ ፕሮግራሙን ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊውን ነገርና ድጋፍ ይፈልጋል። በድስትሪክቶች የሚካሄዱት የትምህርት አሰጣጥ ሂደቶች ልዩነት፣ በድስትሪክቶቹ ውስጥ እንደሚገለገሉት ማህበረሰቦች ልዩነት ነው።

- ፕሮግራሙ እየተሰራ ነው ?
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በድስትሪክቱ ውስጥ ባሉት የትምህርት ፕሮግራሞች እንደሚጠበቅባቸው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታና ብቃት እያገኙ ነው ?



# *የማህበረሰብ መረጃ - 2009*

*"ስብጥር ፈትል የእጅ ሥራ ጥበብን እንደሚያሳምር ሁላችንም ማወቅ አለብን፤ እንደዚሁም ሁሉም ስብጥር ፈትሎች በቀለም ቢለያዩም ጥቅማቸው እኩል እንደሆነ መገንዘብ አለብን።"*

*~ማያ አንጀሎ (~Maya Angelou)*

ጠቅላላ የተማሪ ብዛት፤ 51,460

ጠቅላላ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ብዛት ('ELL')፤ 4,566 ከጠቅላላ ህዝብ 8.87%

| | 'ELL' | የ 'ELL' ብዛት በ% | 'ELL' ያልሆኑ | 'ELL' ያልሆኑ በ% |
|---|---|---|---|---|
| ነጻና ቅናሽ ምሳ | 243 | 5.32% | 10,978 | 23.41% |
| ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች | 36 | .788% | 3,132 | 6.67% |
| ከሌላ አገር የመጡ | 27 | .591 | 0 | 0% |
| ልዩ ትምህርት | 324 | 7.09% | 5,045 | 10.76% |
| በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁ ያልሆኑ ተማሪዎች | 1,396 | 30.57% | | |
| ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ያላቸው ተማሪዎች | 1,930 | 42.27% | | |
| ሙሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች | 1,240 | 27.16% | | |

**በቼሪ ክሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቋንቋዎች**

| | | |
|---|---|---|
| እፍንግሊዝኛ/English | 46,894 | 91.13% |
| ስፓኒሽ/Spanish | 2,334 | 4.54% |
| ኮሪያ/Korean | 378 | .734% |
| ራሺያ/Russian | 228 | 0.443% |
| ቻይና፣ ማንዳሪን/Chinese, Mandarin | 52 | 0.101% |
| አራብኛ/Arabic | 196 | 0.3809% |
| ቪየትናሚስ/Vietnamese | 177 | 0.344% |
| አማርኛ/Amharic | 145 | 0.2818% |
| ሶማሊኛ/Somali | 76 | 0.1477% |
| ሌሎች ቋንቋዎች | 980 | 1.90% |

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ብዛት፣ በቋንቋ




## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ብዛት በብቃት ደረጃ



***"እርስ በራሳችን የሚንቀባበለው ወይም የሚንከባበረው አሁን ባለው ሁኔታችን ላይ በመመሰረት ሳይሆን ወደፊት መሆን የሚንችለውንና ያለንን እምቅ ኃይል በማሰብ ነው።"***

***~ሄንሪ ዴቪድ ዞሪው***

***የመጀመሪያ መለያ***

በቼሪ ክሪክ ውስጥ ከእንግሊዝኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ ለሚናገር፣ ለሚረዳ፣ እና/ወይም ለሚ(ት)ጽፍ ተማሪ ሲ(ት)መዘገብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎቶች የግምገማ ፈተና ይሰጣል።



***ቀጣይ መለያ***

በወቅቱ ያለ/ች ተማሪ ከአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያም በላይ የብቃት ደረጃው/ዋ ሁኔታ ጥራጥሬ ውስጥ ከገባ፣ የተማሪው/ዋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት በመመዘኛ ፈተናው ተገምግሞ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ ይደረግለ(ላ)ታል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ የመገመገሚያ ፈተና በወላጅ፣ በአስተማሪ፣ ወይም ከተማሪው/ዋ ጋር አብሮ የሚ(ት)ሰራ በሌላ የትምህርት ቤት የሥራ ባልደረባ ሊጠየቅ ይችላል። ጥያቄው ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያ ከቀረበ በኃላ፣ የተማሪው/ዋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት/ችሎታ በተዘጋጀው የመመዘኛ ፈተና ይገመገማል/ትገመገማለች።

## ፍሰት ሰንጠረዥ

*ማን:* ወላጅ ወይም አሳዳጊ

*ምን:* አዲስ ተማሪን በድስትሪክቱ ያስመዝግቡና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪን ፎርም/ቅጽ ይሞላሉ፣ የቤት ቋንቋ ዳሰሳን የሚመለከት ቅጽ ነው። ***(ተጨማሪ መረጃ ሀ)***

*የት:* የድስትሪክት መመዝገቢያ ቢሮ

*መቼ:* በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ውስጥ የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በፊት

---

*ማን:* ሁሉም የ 'Lau' ምድቦች ተማሪዎች ሆነው፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቅጽ ላይ 'A-D' ያለበት።

*ምን:* የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት መለያ መመዘኛ ፈተና ይወስዳሉ።

*የት:* በተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት።

*መቼ:* ከተመዘገቡ በሁለት ሳምንታት ውስጥ *ወይም* ከጥቅምት 1 በፊት ከተመዘገቡ ከተመዘገቡ በ 30 ቀናት ውስጥ።

እና

*ማን:* የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምሁራንና አጠቃላይ አስተማሪዎች

*ምን:* ተማሪው/ዋን በተገቢሁ ሁኔታ ለመመደብ አብረው ይሰራሉ።

*የት:* በተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት።

*መቼ:* ከተመዘገቡ በሁለት ሳምንት ውስጥ *ወይም* ከጥቅምት 1 በፊት ከተመዘገቡ ከተመዘገቡ በ 30 ቀናት ውስጥ።

---

*ማን:* የተገምጋሚው/ዋ ተማሪ ወይም አሳዳጊ።

*ምን:* የልጃቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃና ተማሪው/ዋን ለመደገፍ ያሉት አማራጭ ፕሮግራሞችን የሚገልጽ ደብዳቤ በሚፈልጉት ቋንቋ ያገኛሉ።

*የት:* በቤት፣ በልጁ/ጇ ትምህርት ቤት፣ ወይም በውይይት ጊዜ።

*መቼ:* ለተማሪው/ዋ ተገቢው ምደባ ከተደረገ በኃላ።

---

*ማን:* አዲስ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ።

*ምን:* ለተማሪው/ዋ ሊደረግ የታቀደውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍ አለመቀበልን በተዘጋጀው ቅጽ ላይ በፍርማ ማረጋገጥ።

*የት:* ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያ፣ ከአጠቃላይ አስተማሪዎችና ከአስተዳደር ጋር በሚደረገው ውይይት ላይ።

*መቼ:* በየዓመቱ ሆኖ የተማሪው/ዋ መሻሻል ከተገመገመና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍ መስጠት ሀሳብ ከቀረበ በኃላ።

* የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋንና የይዘት ትምህርትን የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

ወይም

*ማን:* ለአዲስ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ።

*ምን:* የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍ ይሰጣል።

*የት:* በተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት።

*መቼ:* በመደበኛ የትምህርት ጊዜ።

*"እልና ሁልጊዜ የተሻለ ሥራን ለመስራት ከሚደረግ ጥረት የሚመነጭና ሂደታዊ የሆነ ውጤት ነው።"*

***~ፓት ሪሊይ***

ትክክለኛ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራም ምደባ የሚደረገው በተለያዩ የግምገማ ውጤቶች ላይ በመሞርኮዝ ነው። ትክክለኛ የተማሪው/ዋ የትምህርትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ የግምገማ ውጤት ትንተና፣ ለተማሪው/ዋ ተገቢና አስተማሪ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴን ለመቀየስ ይረዳል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መረጃ የሚተነተነው እንደ የትምህርት ቤቱ ግቦችና ኃላፊነቶች ክፍል ተደርጎ ነው። መደበኛና ኢመደበኛ የሆኑ የመረጃ ምንጮችን በመከለስ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ላሉት ተማሪዎች በሙሉ ጠቃሚና ውጤታማ የሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ለመቀየስና ለመተግበር ከክፍሉ መምህራን፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ምሁራን፣ የይዘት ዙሪያ አስተማሪዎችና የመማር ማስተማር አስልጣኞች በጋራ ይሰራሉ።

---

**ግምገማ**

በገጽ 16 ላይ ያለው ***የግምገማ ምንጭ*** የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ማስተማር ሁኔታን ለመከታተል፣ በሂደት በትምህርቱ የሚያሳዩትን መሻሻል ለመቆጣጠር፣ ዓመታዊ የቋንቋና የትምህርት ዕድገታቸውን ለመገምገም ሊረዳ የሚችል የቦርዱ የግምገማ ስፋት ያመላክታል። ይህ መጠነ-ሰፊ የሆነ ግምገማ መማር ማስተማርን ግልጽ ከሆኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የግምገማ ውጤቶች ጋር በማዋሄድ የድስትሪክቱን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ግቦች ላይ መድረስ ለመገምገም ይረዳል።

ከተማሪዎች ጋር ሲሰሩና እድገታቸውን ሲመለከቱ፣ የክፍሉ መምህር፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎችና የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች መረጃን ከኮሎራዶ የተማሪ መገምገሚያ ፕሮግራም፣ የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መገምገሚያና ተከታታይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ማጣሪያ ውጤቶች ያገኛሉ። መረጃውን ለመጠቀም ድስትሪክቱ ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣል። ትኩረት የሚሰጣቸው ጥያቄዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤ በክፍለ ግዛቱ ዓመታዊ የሥራ ክንውን አፈጻጸም ግቦች መሰረት፣ ተማሪው/ዋ የኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራምና የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መገምገሚያ የእድገት ግቦች ላይ ደርሷል/ደርሳለች? የማሪው/ዋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ/ብቃት እየተሻሻለ ነው (ቢያንስ በየትምህርት ዘመኑ አንድ ደረጃ እየጨመረ ነው)?

---

**ክትትል**

የተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ የመጻፍና ጠቅላላ የቋንቋው የግንዛቤ ብቃት ለመወሰን፣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክ በየዓመቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን ይጠቀማል።

የማስረጃዎቹ ሰንጠረዥ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ክትትል የሚረዳ ***(ተጨማሪ መረጃ ለ)*** አስፈላጊውንና አማራጭ የተለያዩ የመረጃዎች ስብጥር ይገልጻል። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ጊዜ ሁሉ እነዚህ እርምጃዎች ሥራ ላይ መዋል አለባቸው።

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን መገምገም

ማስረጃዎቹ በድስትሪክቱ የመረጃ ማዕከል ላይ የተከማቹ ሆኖ፣ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን ያካተተ ነው፤

- ዓመታዊ የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት መገምገሚያ ፈተና (ቴስት) (ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ያስፈልጋል)
- ሥርዓተ-ትምህርትን መሰረት ያደረጉ ሚዘናዎች
- መደበኛ ወይም ኢመደበኛ የሆኑ ይዘት ላይ ያተኮሩ የክንውን ፈተናዎች (ቴስቶች)
- የማጣሪያ ፈተናዎች(ቴስቶች)
- የእድገት ወይም የክንውን መስፈርት ዝርዝሮች
- በምልከታና በየቀኑ በሚወሰደው ማስታወሻ የተደረጉት አስተውሎቶች
- የቋንቋ ናሙናዎች፣ የዳሰሳ ጥናቶችና የቋንቋ ብቃት መመዘኛ ፈተናዎች(ቴስቶች)
- የወላጅ፣ የመምህር፣ ወይም የተማሪ መጠይቆች
- የተማሪ ዕለታዊ የትምህርት ክትትል ማስታወሻ
- ማስታወሻዎች ወይም ዕለታዊ ዘገባዎች

---

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎችን መሰረት ያደረጉ ዝርዝር መስፈርቶች**

ድስትሪክቱ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታዎች የብቃት ሂደት ክትትል የሚረዳ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎችን መሰረት ያደረገ ዝርዝር መስፈርቶችን ይጠቀማል። አጠቃላይ መምህራንና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች በጋራ ሆነው ሥራቸውን ሲያቅዱና የበለጠ የመማር ማስተማር ዘዴን ሲያዘጋጁ ይህ የክትትል ሂደት ጠቃሚ ነው።



## የግምገማ እቅድ- መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መጻፍ

| ቴስት | ዓላማ | ዓይነት | የሚሰጥበት ጊዜ | የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት – ምን ምን ያካትታል ? |
|---|---|---|---|---|
| የኮሎራዶ ተማሪ የግምገማ ፕሮግራም | ማንበብ፣ መጻፍ፣ ሒሳብ (3-10)<br>Science (5, 8, 10) | አጠቃላይ | ጸደይ | ማንበብ፣ መጻፍ |
| የኮሎራዶ የምደባ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ግምገማ | ለማስተማሪያ<br>ለምደባ (መዋዕለ ህጻናት-12) | ተከታታይ | በድስትሪክት ውስጥ ካስመዘገቡ በ30 ቀናት ውስጥ፣ ወይም ከጥቅምት 1 በኃላ ከሆነ በ 2 ሳምንታት ውስጥ፣ ይህ የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ላልሆነ ተማሪዎች ነው። | መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መጻፍ |
| የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መስፈርት ዝርዝር | እድገትን መወሰን | ዝርዝር መስፈርት | መጸው፤ ህዳር/ ተህሳስና፣ ፀደይ፤ ሚያዚያ/ግንቦት | መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መጻፍ |
| የምንባብ ችሎታ መመዘኛ ፈተና 2 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መስፈርት ዝርዝር<br>ከመዋእለ ህጻናት-5 ክፍሎች | ማጣራትና የሂደት ቁጥጥር | በዓመት ሦስት ጊዜ | ምንባብ |
| የሰሜን መዕራብ ገምጋሚዎች ማህበር የትምህርት ሂደት ሚዘና | ምንባብ | መመዘኛ | በነጥብ ላይ ይሞረኮዛል | ምንባብ |
| የተማሪዎች ችሎታ መመዘኛ ፈተና | ንግግራዊ ያልሆነ ችሎታ 3ኛ ክፍል | ምርመራ | መጸው | |
| የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃ መመዘኛ | ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥ፣ መናገር | አጠቃላይ | ጥር | መናገር፣ማዳመጥ፣ ማንበብ፣ መጻፍ |

***"ስኬት ጉዞ እንጂ አላማ አይደለም"***

***~በን ስዊትላንድ***

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከፕሮግራሙ ከመውጣቸው በፊት በቋንቋው ያላቸው ችሎታና ብቃት ደረጃ ከሌሎች ተማሪዎች ደረጃ ጋር እኩል መሆኑ ለማረጋገጥ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ነጻ የሆነ የፕሮግራሙ ማጠናቀቂያ መስፈርት አዘጋጅቷል። ተማሪ ይህንን መስፈርቶች ካሟላና በቀጥታ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ የማያስፈልግ ከሆነ፣ቀጥሎ ያለውን አስፈላጊውን ክትትል ለማድረግ የጋራ የውሳኔ ሂደት ይደረጋል።

**ሂደት፤**

- የሂደት ክትትል የሚጠቁመው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ በተከታታይ፤
  - በአራቱ የቋንቋ ክህሎቶች፤ መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብና መጻፍ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማሳየት።
  - በቋንቋ ሥነ-ጥበብ፣ በሳይንስ፣ በማህበራዊ ሳይንስና በሒሳብ ትምህርቶች የሚፈለገውን ብቃት ማሳየት።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያ ከይዘት አስተማሪዎች፣ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ እንደዚሁም ከተማሪ ጋር በመተባበር፤
  - ከውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ወደ ቆልጣፋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማሻገር ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ መረጃዎችን ከተረጋገጡና ሁነኛ ከሆኑ ግምገማዎችና ከተሰናዱ አስተውሎቶ ውሁቦችን/እውነታዎችን ያሰባስባሉ፣ እንደዚሁም የተገኘውን መረጃ ትርጉም ባለው መልክ ያቀናጃል/ታቀናጃለች።
  - በመረጃዎች ስብስብ ውስጥ የተካተቱትን መረጃዎች በድስትሪክቱ የመረጃ ማዕከል ውስጥ ያሰናዳል/ታሰናዳለች።
  - ተማሪ ቆልጣፋ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ መሆኑ/ኗን የሚገልጽና ቀጣይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ እንደማያስፈልገው/እንደማያስፈልጋት የሚገልጽ ደብዳቤ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ይሰጣል/ትሰጣለች።
  - ተማሪው/ዋ በአጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም ያለውን/ያላትን ስምረት ለመወሰን ለሁለት ዓመታት የተማሪው/ዋን ተለውጦ ይገመግማል/ትገመግማለች።
  - በሁለት ዓመት የግምገማ ጊዜ ውስጥ የተማሪው/ዋ የትምህርትና የሥነ-የቋንቋ ስምረት ከታመነበት ተማሪው/ዋ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ ፕሮግራም በደንቡ መሰረት እንዲ(ት)ወጣ ያደርጋል/ታደርጋለች።
- ትምህርት ቤቶች ተማሪው/ዋ እንግሊዝኛ ቋንቋን ሲ(ት)ማር የሌሎች ትምህርቶችን መዛባት ችግር ለማስተካከል የሚያስፈልግ ማንኛውንም ዓይነት ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

**ለየት ያሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንደገና መመደብና ከፕሮራሙ ማስወጣት**

ልዩ የትምህርትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ የሚደረግለትን/የሚደረግላትን ተማሪ እንደገና የመመደብ ውሳኔ የሚደረገው በልዩ ትምህርት ፕሮግራም አባላት ቡድን (የልዩና የጠቅላላ ትምህርት መምህራን፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያ፣ ወላጆችና ተማሪው/ዋ) እንደዚሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪው/ዋንና ክንዋኔው/ዋ በሚያውቁ ሌሎች ግለሰቦች ነው። የተማሪ ስንኩልነት የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደገና ምደባ/ማጠናቀቂያ መስፈርት ማሟላት የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ በተማሪው/ዋ ፍላጎት ላይ በመመስረት ተገቢውን የድጋፍ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ቡድኑ በተማሪው/ዋ ሰነድ ላይ በመስማማት የመረጃ ስብስብ ያሰናዳል። ይህ የመረጃ ስብስብ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤ የተማሪው/ዋን የልዩ ትምህርት ፕሮግራም፣ የትምህርት ባለሙያዎች ጣልቃ በመግባት ሲረዱ ተማሪው/ዋ ሲ(ት)ሰጥ የነበረውን ምላሽ ሰነዶችና/ወይም የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ግምገማ ውጤቶች ናቸው።

## ማለፊያ ያለው ሥርዓተ-ትምህርት

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለሁሉም ተማሪዎቹ ማለፊያ ያለው ሥርዓተ-ትምህርት ለማቅረብ በቁርጠኝነት እየሰራ ነው። ትኩረቱ እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ ለኮሌጅ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ በኃላ ላለው ትምህርት ብቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የቼሪ ክሪክ መመዘኛዎች የሚገልጸው ተማሪዎች አምስተኛ፣ ስምንተኛና አሥራ ሁለተኛ ክፍሎችን ሲያጠናቅቁ ማወቅና መተግበር የሚጠበቅባቸውን ጉዳዮች ነው።

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ማለፊያ ያለው ሥርዓተ-ትምህርት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው የይዘት መመዘኛዎች መለየትን የሚደግፍ በኮሎራዶ ክፍለ ግዛት እንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎች ይደገፋል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያዎች፣ የጠቅላላ ትምህርት መምህራን፣ እንደዚሁም የትምህርት ቤት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎችን በማወቅ በትምህርት ፕሮግራማቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ይደረጋል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎችን ከፈለጉ ቀጥሎ ካለው የኮሎራዶ የትምህርት ቢሮ ድረ-ገጽ ሊያገኙ ይችላሉ፤ http://www.cde.state.co.us/cde_english/download/ELDStandardsApril2005.pdf

### አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከመዋለ ሕጻናት- 5ኛ ክፍሎች

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጻፍና ማንበብ፣ እንደዚሁም የቁጥሮች ችሎታ እድገት ዋና ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ሥርዓተ-ትምህርቱም የተፈጥሮና የማህበረሰብ ሳይንስ መሠረታዊ ችሎታዎችንና ጽንሰ ሐሳቦችን መገንባት ላይ ያተኩራል። የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች  በሥነ ጥበብ፣ በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ በቴክኖሎጂና በሚዲያ ቁሳቁሶች ትምህርታቸውን ያሻሽላሉ።

### መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከ 6-8 ክፍሎች

መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሰረተ-ትምህርት ላይ ይገነባል፣  ይህንን ሲያደርግ በሁለተኛ ደረጃና ከሁለተኛ ደረጃ  በኃላ ላሉት ትምህርቶች ለተማሪ የትምህርት ክንውን ጠንካራ መሰረት መጣልን በማረጋገጥ ነው። ተማሪዎች በምንባብ፣ በጽሁፍ፣ በሒሳብ፣ በሳይንስ፣ በታሪክና በመልክዓ ምድር (በጅኦግራፊ) ትምህርቶች ሰፊና ጥልቅ እውቀት ሊኖራቸው አለባቸው። እንደዚሁም ተማሪዎች እንደ ሥነ ጥበብ፣ ሚዲያ (የዜና ማሰራጫ)  ችሎታዎች፣ የውጪ ቋንቋ፣ ኮምፒዩተር፣ ቴክኖሎጂ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ የጤናና የተጠቃሚዎች እንደዚሁም የቤተሰብ ጥናቶች ያሉ ተጨማሪ ትምህርት ሰጪ የሆኑ ዋነኛ ሥርዓተ-ትምህርት ፕሮግራሞች ሊሳተፉ ይችላሉ።

### ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከ 9-12 ክፍሎች

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሥርዓተ-ትምህርት ተማሪዎች ለኮሌጅ ትምህርትና ለሥራ ዓለም ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ቀጥሎ እንደተዘረዘሩት ሁሉም ተማሪዎች ዋነኛ ትምህርቶችንና ተጨማሪ 20+ ነጥቦች በታች በተጨማሪም የውጪ ቋንቋን ይወስዳሉ።

| 3 ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት፤ | 4 ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት፤ |
|---|---|
| ሒሳብ<br>የማህበራዊ ጥናቶች<br>የተፈጥሮ ሳይንስ | እንግሊዝኛ |

የላቀና ጥብቅ ሥርዓተ-ትምህርት በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መልካም ዜጋን ለማፍራት የሚረዳ 'International Baccalaureate'፣ ለላቀ ደረጃ ለመመደብ የሚረዳ 'Advanced Placement'፣  እና ሌላ 'Honors' በሚባሉ የትምህርት ፕሮግራሞች አማካይነት ይሰጣሉ።

*"ተማሪዎች አንተ/ቺ በሚታስተምርበት ዘዴ ሳይማሩ ሲቀሩ፣ እነሱ በሚማሩበት ዘዴ አስተምር።"*
*- ሜሪ አን ክራይስትሰን*

**ምርጥ የመማር ማስተማር ሂደት**

- የድስትሪክቱን ተልዕኮ ለማስፈጸም ሁሉም አስተማሪዎች፣ ወደፊት በዓለም አቀፍ ምጣኔ ሃብት ውስጥ የሚኖሩና የሚሰሩትን፣ የአሁኖቹንና የወደፊቶቹን ተማሪዎች ለማስተማር እውቀቱንና ችሎታውን እንዳላቸው ማረጋገጥ አለብን። ለዚያ ደግሞ ተማሪዎችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመንና ከዚያ ወዲያም የሚያዘጋጀት ምርጥ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። እንደ ድስትሪክት፣ ከእያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ ጋር በመሥራት እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ እምቅ እውቀቱ(ቷ)ን እንዲ(ት)ጠቀም እንዲያግዙ የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን ድጋፍ ለሁሉም አስተማሪዎች ሙያዊና ቁሳዊ ለማድረግ በቁርጠኝነት እንሰራለን።
- ይህ ምርጥ የመማር ማስተማር እቅድ ለእያንዳንዱ ተማሪ እጅግ በጣም ጥሩ መሰረት ይጣላል። የእያንዳንዱ(ዷ)ን ተማሪ የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት መምህራን ያላቸው ሙያዊ የውሳኔ ነጻነት እንዳለ ሆኖ፣ እቅዱ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የመማር ማስተማር ፈርጆችን ይነድፋል።
- የቼሪ ክሪክ የመማር ማስተማር እቅድ አራት ተያያዥ ፈርጆች አሉት፤ **ማቀድ፣ ማስተማር፣ መገምገምና ማስተካከል** ናቸው። እነዚህ ፈርጆች በተወሰነ ደረጃ የሚደራረቡ ሆነው፣ እቅዱ የሚነድፈው በእያንዳንዱ ፈርጅ ውስጥ በተናጥል ያሉት ዋና ሀሳቦች በቼሪ ክሪክ የአስተማሪ አስተውሎት ሰነድ ጋር ማያያዝ ነው።

**የእቅዱ ዓላማ**

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የመማር ማስተማር እቅድ የሚመሰረተው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልምምድ፣ በተጨባጭ ሁኔታዎችና ቅንጅት ወነች ላይ ነው። እነዚህ ወነች ለተማሪ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ክንውን በጥናትና ምርምር የተረጋገጡ እጅግ በጣም ውጤታማ የሆኑ ዘዴዎች ናቸው።

- በደንቨር፣ ኮሎራዶ ውስጥ ያለ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም የሆነው 'Mid-Continent Research for Education and Learning (McREL)' በሚባለው መሰረት፣ ፣ የተሳካላቸው የትምህርት ድስትሪክቶች አንዱ ምልክት ሰፊ፣ ነገር ግን የጋራ የመማር ማስተማር ቋንቋና ቃላት፣ እንደዚሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረቱ ጽኑ የሆኑ የመማር ማስተማር ስልቶችን ወደ መጠቀም የሚያመሩ፣ የተለመዱ የመማሪያ ክፍል የመማር ማስተማር ዝግጅቶችና እቅዶችን መጠቀም ነው።
- ሌሎች ተመራማሪዎች የሚስማሙት — የተሳካላቸው ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ድስትሪክቶች የትምህርት ይዘቱን፣ የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎችን፣ የማስተማርና የሚዘና ዘዴዎችን የሚገልጽና የሚከተል የመማር ማስተማር እቅድን ያዘጋጃል*(Newman, Smith, Allensworth, and Bryk, 2001)*።
- በ 'McREL'ና በሌሎች ተቋማት ያሉት ተመራማሪዎች ከፍተኛ የተማሪ የትምህርት ክንውን የሚያስገኙ (ለምሳሌ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምርጥ የመማር ማስተማር ሂደት) የተወሰኑ የመማር ማስተማር ልምምዶችን አግኝተዋል። ይህ እቅድ እነዚያን ልምምዶችን በማካተት ከቼሪ ክሪክ የአስተማሪ አስተውሎት ሰነድ ጋር ያገናኛቸዋል።
- የተለመዱ የመማር ማስተማር እቅድን መጠቀም በ2006-2007 የትምህርት ዘመን በተደረገው ጥልቅ የራስ መገምገም ግኝቶች ጋር በጽኑነት መሄድ አለበት። ለዚያ ሂደት ለድስትሪክት የበለጠ የተቀናጀና በደንብ የታሰበበት የመማር ማስተማርና ሥርዓተ ትምህርት ያስፈልጋል።

**ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ከላይ የተዘረዘሩትንና ቀጥሎ ያሉትን ያካትታል፤**

- ይዘትንና ቋንቋን በማዋሃድ ማስተማርን የሚደግፍ የመማር ማስተማር ሂደት የአስተውሎት ሥርዓት (በ Echevarria፣ Vogt፣ እና Short የተዘጋጀ) መሰረት ያደረገ የማስተማር ዘዴ።
- ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚመች የመማር ማስተማር ሂደትን መሰረት ያደረገ የማስተማር ዘዴ (በ Hill እና 'Flynn' የተዘጋጀ)።
- ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማዘጋጀት፣ አገልግሎቶቹን መስጠትና የተሰጡትን አገልግሎቶች መገምገም የሚመለከት መመሪያ ድረ-ገጽ፤ http://www.cde.state.co.us/index_home.htm

## ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ የሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

| ዘዴ | ገለጻ |
|---|---|
| **በቡድን መማር**<br>ዋቢ፡ (Barkley፣ እና ሌሎች፣ 2001፤ Correa እና Tulbert, 1991፤ Ghaith፣ 2003፤ Kagan፣ 2000) | የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ተማሪዎችን በቡድን ማሰራት። ተማሪዎች ለራሳቸውና ለሌሎች መማር ኃላፊነት ይወስዳሉ። ተማሪዎች እንዲወያዩና እንዲረዳዱ ዕድል ይሰጣል። |
| **የይዘትና የቋንቋ ውሕደት**<br>ዋቢ፡ (Chamot እና O'Malley፣ 1987፤ Echevarria፣ Vogt እና Short፣ 2008፤ Lewis-Moreno፣ 2007) | የይዘት ትምህርትን ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማዋሃድ። የይዘትና የቋንቋ ግቦች ይጠቀማሉ። ይዘትን ለማስረዳት አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል። |
| **መነጋገር**<br>ዋቢ፡ (Carrier፣ 2006፤ Twyman, Ketterlin-Geller፣ McCoy፣ እና Tindal፣ 2003፤ Yoon፣ 2007) | ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን የተማሩትን በጋራ እንዲወያዩ ማድረግ። ተማሪዎች የተማሩትን የትምህርት ይዘት እንዲገልጹና ቋንቋን እንዲለማመዱ ይረዳል፣ እግረ መንገዱንም ፍራቻን እንዲቀንሱ ይረዳል። |
| **መግቢያና ተማሪን ከሪዕስ ጋር ማስተዋወቅ**<br>ዋቢ፡ (Goldenberg፣ 2008፤ Hickman፣ Pollard-Durodola፣ እና Vaughn፣ 2004፤ Twyman እና ሌሎች፣ 2006) | ተማሪዎችን ስለትምህርቱ ሪዕስ ጉዳይ የሚያቁትን መጠየቅ። ስለ ሪዕሱ ምንም የማያውቁ ከሆነ፣ አስተማሪው/ዋ የትምህርቱን ሪዕስ አስመልክቶ መረጃ ይሰጣቸዋል/ትሰጣቸዋለች። ይህም ከተሞክሮአቸው/ከልምዳቸው ጋር በማገናኘት ነው። |
| **በግልጽ ማስተማር**<br>ዋቢ፡ (August፣ Carlo፣ Dressler፣ እና Snow፣ 2005፤ Carlo፣ እና ሌሎች፣ 2004፤ Kucer እና Silva፣ 1999፤ McCollin እና O'Shea፣ 2005) | ግልጽ የሆነ ትምህርትን መስጠትና ስለእንግሊዝኛ ቋንቋ መግባቢያዎች፣ ሰዋስው፣ የቃላት አጠቃቀምና ቃላትን በተለያዩ መንገዶች ማስተማር። ይህ ተማሪ የንግግርና የጽሁፍ ችሎታዎችን እንዲያጎለብት/እንዲታጎለብት ይረዳል። |

| ተከታታይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ዕድገት አገልግሎቶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ የብቃት ደረጃዎችን መገምገም | | | | |
| ጀማሪ<br>1 | ጀማሪ መካከለኛ<br>2 | መካከለኛ<br>3 | ብቁ<br>4 | ከብቁ በላይ<br>5 |
| በሌላ ቋንቋ ብቃት ያለው/ያላት | | ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያለው/ያላት | | በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ያለው/ያላት |
| በአቅድና በማስተማር ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች | | | | |
| መማር ማስተማሩ የክፍል ደረጃውን ሚዘናዎች ያሟላል፣ እንደዚሁም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የይዘት ትምህርት ይሰጣል፣ በዚያም ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ።<br>የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎችና የክፍሉ/የይዘት ትምህርት መምህራን የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ትምህርት ይሰጣሉ። | | ከክፍል መምህራንና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች የሚገኘው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በትምህርት ይዘት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያስፈልጋቸውን አስፈላጊውን የስነ-ቋንቋ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።<br>የክፍል መምህራን፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎች፣ እንደዚሁም ሰራተኞች ባለው መረጃ መሰረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁ ላልሆኑ ተማሪዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ። | | የሁለተኛ ደረጃ የይዘት ትምህርት ዙሪያ መምህራንና የአንደኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት መምህራን የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ትምህርት ይሰጣሉ። |
| በጋራ ማስተማር የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎችና የክፍል ደረጃው የይዘት መምህራን በጋራ ማስተማር የይዘት እውቀትና የቋንቋ ትምህርትን ለማዋሃድ ስለሚረዳ በጣም ይደገፋል። | | | | |
| ሌሎች ተጨማሪ ፕሮግራሞች እንደአስፈላጊነታቸው የሚታሰቡበት ይሆናል | | | | |
| የአጭር ጊዜ አዲስ መጪ ፕሮግራም ማዘጋጀት (ለአዲስ መጪዎች፣ ለጀማሪዎች፣ እና/ወይም ለስደተኞች) ፤ ይህ ፕሮግራም እንደነዚህ ያሉ ተማሪዎች ትምህርት ቤትን እንዲለምዱና መሰረታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎችን እንዲቀስሙ ይረዳል። | | | | |
| **በሁለተኛ ደረጃዎች፣ ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ፣ በተጨማሪም፤** በይዘት ትምህርትና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የሰለጠኑና ሙያዊ የምስክር ወረቀት ባላቸው መምህራን የተዋሃዱ የይዘትና የቋንቋ ትምህርቶች ይሰጣሉ። | | | | |
| የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ። | | | | |
| ሌሎች ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች | | | | |
| በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ ስልጠናና ልምድ ያላቸው መምህራንን መቅጠር።<br>መምህራን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።<br>መምህራን በስትሪክት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ስልጠና እንዲሳተፉ እና/ወይም ከመማር ማስተማር አሰልጣኞች ጋር እንዲሰሩ ማበረታት። | | | | |

*“አስተማሪ ራሱን/ራሷን መስዋእት እያደረገ/ች ለሌሎች የለውጥ ምክንያት የሆነ ዜጋ ነው።”*
*~ቶማስ ካሩተርስ*

ከሁሉም በፊት፣ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተወላጅ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችና ጣልቃ በመግባት የሚደረጉ ልዩ ድጋፎች በሙሉ በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ላሉት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችም ይሰጣል። እነዚህም ‘Title I’ የሚባል ፕሮግራም (የፌዴራል መንግሥት በተለይ በምንባብና በሒሳብ ትምህርቶች ደከም ላሉ ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ የሚሰጥበት ፕሮግራም ነው)፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎት፣ ወይም ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጡ ልዩ ድጋፎች አገልግሎቶችን ያካትታል። ይህ ጉዳይ ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ወይም በትምህርታቸው የሚችገሩ ተማሪዎችን አስፈላጊውን መዋቅርን ዘርግቶ ጣልቃ በመግባት ለመርዳት በፌዴራል መንግሥት የሚደጎመውን የ ‘Title I’ እና የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችን፣ እንደዚሁም በክፍለ ግዛትና በድስትሪክት የሚደገፉ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍ ማግኘት ለተማሪ አስፈላጊው የምንባብ፣ የሒሳብ፣ ወይም የጽሁፍ ጣልቃ-ገብ ድጋፍ እንዳይሰጥ ላይከለክል ይችላል።**

የጣልቃ-ገብ ድጋፍ ፕሮግራሙ ወይም ሥራ ላይ የዋለው ሞዴል እንዳለ ሆኖ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተወላጅ ተማሪዎች መካከል ያለውን የትምህርት ክንውን ክፍተት ለመዝጋት ቀጥሎ ያሉትን ሊሰሩበት የሚችሉና የተረጋገጡ ልምምዶች ማካተት እንደግፋለን።

- አቀፋው ሚዘና/ምርምራ
- ይዘትንና ቋንቋን በማዋሃድ ማስተማር (አዳዲስ ቃላትን ተማሪዎች ከሚያውቁት ጉዳዮች ጋር በማገናኘት ማስተማር)።
- ተከታታይ የተለውጠ ግምገማና ዘላቂ የተማሪ እድገት ተጠያቂነት።
- በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱትን ጨምሮ፣ ባህልና ቋንቋን ማዕከል ያደረጉ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረቱ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም።
- ከጠቅላላ መምህራን፣ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎች፣ ከሌሎች ፕሮግራሞች ባለሙያዎችና ከወላጆች ጋር አብሮ መስራት።

---

**ለጣልቃ-ገብ ድጋፍ ተማሪዎች የሚሰጡት ምላሽ**

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ሁሉም ተማሪዎች ለጣልቃ-ገብ ድጋፍ የሚሰጡት ምላሽ ከድስትሪክቱ እቅድ ጋር ይሄዳል - ማስተማር-መገምገም-ማስተካከል፤ ምርጥ የመማር ማስተማር ሂደት ናቸው። **ይህ ሂደት አስተማሪዎች መማር ማስተማርን ማቀድና ውጤታማ የሆነ ትምህርትን መስጠትን፣ መገምገምና በተከታታይ መቆጣጠር፣ እንደዚሁም በጽኑነት ጣልቃ እየገቡ መገምገምን ይፈልጋል።** አስተማሪዎች ጊዜያቸውን የሚያተኩሩት በተማሪ መማር፣ በተማሪ ግምገማና በተማሪ መማር ውስጥ ጣልቃ እየገቡ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት።

- በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በጊዜው ፍትሃዊ የሆነና አግባብ ያለውን የማሚያ ጣልቃ-ገብ ድጋፎችን ለተማሪዎች ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር መዘርጋት አለበት። ይህ ጉዳይ በመደበኛ የትምህርት ቤት ጣልቃ-ገብ መዋቅራዊ ድጋፎች ወይም በግላዊ ችግር መፍታት ሂደት ሊፈጸም ይችላል።

- የችግር መፍታት ወይም ጣልቃ መግባት እቅድ ቡድን ተገቢውን ጣልቃ መግባቶች ከቤተሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ በማግኘት የተማሪን ቋንቋና ባህል ከግምት ማስገባት አለበት።

- የትምህርት የክንውን ክፍተትን ለመዝጋት፣ የማሪው/ዋ የተወላጅ ቋንቋ እድገት፣ የመጻፍና የማንበብ ችሎታና ጠቅላላ የትምህርት ችሎታዎቹ/ቿ እንዳሉ ሆነው፣ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚመረጡ ጣልቃ-ገብ ድጋፎች ውጤት ተኮር፣ ጥብቅና የክፍል ደረጃውን ሥርዓተ-ትምህርት የሚያሟሉ ናቸው።

- እነዚህ ጣልቃ መግባቶች ለክፍል ደረጃው አስፈላጊ የሆነ ሥርዓተ-ትምህርት ለመስጠት፣ እንደዚሁም ጥብቅ የሆነውን የክፍል-ግዛት መመዘኛዎችን ለማሟላትና ለተማሪዎች ፍትሃዊ የሆነ የመማር እድል ለመስጠት የሚረዱ ለቃላት፣ ለችሎታዎችና ለጽንሰ ሀሳባዊ እውቀት ትምህርቶች ቀጥታ ማስተካከያና ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣሉ። በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ተማሪ ለጣልቃ-ገብ ድጋፍ በቂ ምላሽ ሳይሰጥ ሲ(ት)ቀር፣ ዋነኛውን ትምህርት ማሟላት ሳይሆን መተካቱ አግባብ ያለው ተግባር ነው።



**ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለየ ትምህርት አሰጣጥ ውስጥ መመደብ፤**

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለጣልቃ-ገብ ድጋፍ የሚሰጠውን ምላሽ መረጃ ጨምሮ፣ በተለያዩ የተማሪ የትምህርት ክንውን መረጃዎች ላይ በመመሰረት፣ የተለየ ትምህርት አገልግሎቶችን ሊያገኙ ይችላሉ።
- ለወላጆች ስለመብቶቻቸው፣ ስለልጆቻቸው መብት፣ ስለሰራተኞች የቅጥር ሂደትና በምደባ ሂደት ውስጥ ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች ሁሉ ይገለጹላቸዋል።
- ተማሪ በተለየ ትምህርት ውስጥ ሲ(ት)መደብ፣ ለተማሪው(ዋ) ወላጅ ምደባው ለምን እንዳስፈለገ ይገለጽላቸውና ስለጉዳዩ ከሚመለከተው ከትምህርት ቤት ሰራተኛ ጋር እንዲወያዩ እድል ይሰጣቸዋል።
- ከወላጆች ጋር የሚደረጉ ሁሉም ግንኙነቶች የሚካሄዱት ወላጆች በሚፈሊጉት ቋንቋና ሁኔታ ይሆናል።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ባለሙያ በግላዊ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ በንቃት ይሳተፋል/ትሳተፋለች።
- ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ የሚሰጡ የሚዘና ፈተናዎችን ገምግሞ ሁነኛ (የሚታመኑ) እና የተረጋገጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።
- ተማሪዎች የልዩ ትምህርት ድጋፍ ሲያገኙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ድጋፍም በቀጣይነት ያገኛሉ።

---

**ተማሪን በክፍል ደረጃው(ዋ) መያዝ(ማቆየት)፤**

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማነስ ምክንያት ብቻ በክፍል ደረጃቸው ውስጥ መቆየት የለባቸውም። የአሜሪካ ጠቅላይ ክፍለ ግዛቶች ትምህርት ቢሮ ይህንን ሁኔታ ከተፈጠረ ጉዳዩን እንደ መድልኦ ይወስደዋል፤ ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልምድ ስለለላቸው ብቻ ክፍል ደረጃቸው ውስጥ እንዲቆዩ በመደረጉ ነው።ተማሪን ክፍል ውስጥ ማቆየት ማሳሰቢያ በተመለከተ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች መመሪያ አለው።

## ሙያዊ ዕድገት

*ለማስተማር የሚደፍር ከመማር ወደ ኃላ አይልም።~John Cotton*

| ትኩረት የሚሰጡባቸው ጉዳዮች | የሙያዊ ዕድገት ግቦች | ወቅታዊ የሙያዊ ዕድገት እድሎች | የታቀዱ የሙያዊ ዕድገት እድሎች |
|---|---|---|---|
| መለየት/ መመደብ እንደገና መለየት በከፍል ደረጃ ማቆየት | የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪዎች (የይዘት፣ የዋነኛ ትምህርት ዓይነትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎችን ጨምሮ)<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመለየትና የመመደብ ሂደት<br>• የተወላጅ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችንና የሌሎች ተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ፍላጎትን መረዳት።<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ባህሪዎችና ልዩ የትምህርት ፍላጎቶችን ማወቅ።<br>• በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁ የሆኑ፣ 1ኛ ደረጃ ክትትልና ግምገማ የሚደረግላቸው፣ 2ኛ ደረጃ ክትትልና ግምገማ የሚደረግላቸውና ፕሮግራሙን ካጠናቀቁት ተማሪዎች ጋር ሲሰሩ አስተማሪዎች ዓይነተኛ ሚናቸውን ማወቅ አለባቸው። | • በኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሚዘናና ምደባ ሂደት የሰለጠኑ ሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች።<br>• ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ባህሪያትንና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመለየት የሚረዳ የመረጃ አተናተን አስመልክቶ በየዓመቱ ሥልጠና የሚያገኙ የልዩ ተሰጥኦ አስተማሪዎች።<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመለየት፣ የመመደብና እንደገና የመመደብ ፖሊሲና ሂደቶችን አስመልክቶ ሥልጠና ያገኙ ሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎች። | • የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን(የይዘት፣ የዋነኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች ጨምሮ) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ተማሪዎችን የመለየት፣ የመመደብና እንደገና ለይቶ የመመደብ መስፈርቶችን አስመልክቶ ሥልጠና ያገኛሉ።<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ምደባና እንደገና ለይቶ የመመደብ ፖሊዎችና ሂደቶችን ለመወያየት ለወላጆች ዕድል ይሰጣል። |
| ሚዘናና ግምገማ | የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት፤<br>• ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የሚሰጡ የሚዘናና ግምገማ ተግባራት ጽኑነትን ያረጋግጣል።<br>• የመስማት፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎቶችን ለመከታተል የሚረዱ የጋራ ሚዘናዎችን ያዘጋጃሉ።<br>• በትምህርት ቤት ፍላጎቶች ላይ በመመሰረት የሙያዊ እድገት ሥልጠናን ለይቶ መስጠት። | • የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎች የመማር-ማስተማር ሂደቶችንና ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ያለውን ትርጉም አስመልክቶ ወራዊ የድስትሪክት ሥልጠና ይወስዳሉ።<br>• የድስትሪክት ሙያዊ ሥልጠና ዕድሎች የሚሰጡት በሚዘናና ግምገማ ቢሮ ሆኖ ሥልጠናው በመረጃ ትንተና ዙሪያ ላይ ያተኩራል። | • ሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚረዳ ተከታታይ ሙያዊ እድገትና ሥልጠናን በአስፈላጊና መሰረታዊ የመማር ማስተማር ፈርጆች ዙሪያ ይወስዳሉ።<br>• በድስትሪክት እንደተወሰነው ሁሉም አስተማሪዎች ተከታታይ ኮርሶችን(በኮምፒዩተር በመታገዝ ወይም በአካል በቦታው በመገኘት)ማጠናቀቅ አለባቸው። |

| ትኩረት የሚሰጡባቸው ጉዳዮች | የሙያዊ ዕድገት ግቦች | ወቅታዊ የሙያዊ ዕድገት እድሎች | የታቀዱ የሙያዊ ዕድገት እድሎች |
|---|---|---|---|
| ሥርዓተ-ትምህርትና መማር- ማስተማር | የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪዎች(የይዘት፣ የዋነኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎችን ጨምሮ)፤<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ልዩ ፍላጎት የሚያሟሉ የትምህርት አሰጣጦችን፣ ተግባራትንና ዘዴዎችን ይረዳሉ<br>• ለተሻለ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማር ማስተማር የሚረዱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ይረዳሉ<br>• የቋንቋ ትምህርት ንድፈ ሐሳብንና የቋንቋ ትምህርት በሌሎች ትምህርቶች ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ይገነዘባሉ<br>• የታወቁ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥያሜዎች/ቃላት በተመለከተ መሰረታዊ ግንዛቤ ያገኛሉ | በድስትሪክት የሚሰጡ የተለያዩ የሥልጠና/የኮርስ ዓይነቶች፤<br>• መሰረታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ባሻገር በጋራ ማስተማር<br>• ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍና የማንበብ ትምህርትን ማሻሻል<br>• ለአስተዳደሮችና ለመማር ማስተማር ሰራተኞች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሥልጠና መስጠት<br>• በዋነኛው ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ ይዘትንና ቋንቋን በማቀናጀት ማስተማር<br>• የየእለቱ የትምህርት መረጃ (ማስታወሻ)፤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የትምህርት ክንውን ለማሻሻል በሥር ዓተ-ትምህርት ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች(ምን ምን?)፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት (እንዴት?) እና የትምህርቱ ጊዜ (መቼ?)<br>• በመማር ማስተማር ሥልጠና አማካይነት ውጤቶችን ማግኘት | በድስትሪክት ደረጃ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰጡ ኮርሶችንና ድጋፎችን ያካትታል፤<br>• የማስተማር ማስተማር ሥልጠና<br>• የባለሙያዎች ማህበረሰብ ሥልጠናን ማመቻቸት<br>• የትምህርት ቤት ደረጃ በደረጃ ገለጻዎች<br>• ከባለሙያ ማህበረሰብ ጋር የማጥናት ዕድሎች<br>• ይዘትንና ቋንቋን አቀናጅቶ የማስተማር ሥልጠና<br>• የበጋራ ማስተማር ሥልጠና<br>• የመረጃ እሰጥ አገባና ትንተና |
| የወላጆች ተሳትፎ | የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪዎች(የይዘት፣ የዋነኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያዎችን ጨምሮ)፤<br>• ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቤተሰቦች ጋር በጋራ እንዴት እንደሚሰሩ ይገነዘባሉ<br>• በቤት ውስጥ የተወላጅ (የቤት) ቋንቋን መጠቀም አስፈላጊነት ይረዳሉ<br>• ከወላጆች ጋር በባህላቸውና በቋንቋቸው መሰረት በመተባበር ልጆቻቸውን በቤት እንዴት በትምህርታቸው እንደሚረዷቸው መወያየት | • በየትምህርት ቤቶቹ ያሉት የወላጆች ተሳትፎ ዕድሎች<br>• የድስትሪክት ሙያዊ እድገት እድሎች በፍትሃዊነትና ከባህል ጋር የሚሄዱ መማር ማስተማር ላይ ያተኩራሉ<br>• የአስተዳደር ሥልጠና በፍትሃዊነትና ከባህል ጋር የሚሄዱ መማር ማስተማር ላይ ያተኩራሉ | • ድስትሪክት ለሁሉም ሰራተኞች በሚሰጠው ሥልጠና አማካይነት ቀጣይ ሙያዊ ዕድገት<br>• የቤተሰብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ትምህርት ማዕከል ፕሮግራምን በድስትሪክቱ ሌሎች ትምህርት ቤቶችም ማስፋፋት<br>• ፍትሃዊነትንና ባህል-ነክ የሆኑ ሥርዓቶች፣ እሴቶችና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ ለሁሉም የድስትሪክት ሰራተኞች የሚሰጠውን ወቅታዊ ሥልጠና ማስፋፋት(አስተዳዳሪዎች፣ የጥበቃ፣ የመመዝገቢያ ቢሮ፣ ወዘተ ሰራተኞችን ያካትታል)<br>• የፍትሃዊነት ጉዳዮችን ከእውቀት ወደ ተግባር መለወጥ |

| ትኩረት የሚሰጡባቸው ጉዳዮች | የሙያዊ ዕድገት ግቦች | ወቅታዊ የሙያዊ ዕድገት እድሎች | የታቀዱ የሙያዊ ዕድገት እድሎች |
|---|---|---|---|
| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ወላጆች፤<br>● ለልጆቻቸው ያሉትን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አማራጭ ፕሮግራሞች ይረዳሉ<br>● ተማሪን ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም መለየት፣ መመደብና እንደገና የማጣራት ሂደቶችን ይረዳሉ<br>● እንደወላጆች ልጆቻቸውን በትምህርታቸው ሲረዷቸው መብቶቻቸውንና ኃላፊነቶቻቸውን ይረዳሉ | | ● በድስትሪክቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች የፍትሃዊነት ጉዳዮችን በተመለከተ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ |



***"በነ አመለካከት፣ የሰው ልጅ ሥልጣኔ የሚለካው በህንጻ ትልቅነት ሳይሆን፣ ህዝቦቹ ከአካባቢያቸውና ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም መኖር በመቻላቸው ነው።"***

***-'Sun Bear' የሚባል የችፓዋ ጎሳ***

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ዓላማ ወላጆች ከልጆቻቸው ትምህርት ቤቶች ጋር እንዲገናኙና የተለያዩ ባህልና ቋንቋ ካላቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ማበረታት ነው። በትምህርት ቤትና በድስትሪክት ደረጃ ያለው የወላጆች ተሳትፎ የሚበረታታው ትርጉም ያለውና ጽኑና ውጤታማ የሆነ የግንኙነት ሂደት አማካይነት ጠቃሚ መረጃዎችን ለወላጆች በመስጠት ነው።

የትምህርት ቤት ወኪሎች ለወላጆ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጡት ወላጆችን በትምህርት ቤት ተግባራት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች መሳተፍ እንደሚችሉ በማበረታታት ነው። ወላጆች በትምህርት ቤቶች የሚሳተፉባቸው መንገዶች ምሳሌዎች እነሆ፤

- በትምህርታቸው የተሳካላቸው ተማሪዎች ማህበር
- የወላጅ መምህር ማኅበረሰብ ድርጅት
- የትምህርት ቤት ተጠያቂነት ኮሚቴ
- የትምህርት ቤት መመለሻ
- የወላጅ ውይይት
- የወላጅ አመራር ቡድን

***መከባበርና መተሳሰብ የበዛበት ቦታ እንዲሆን ያሉ ግቦች/ዓላማዎች***

1. ወላጆች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንዲረዱ የሥልጠና ዕድሎችን መፍጠርና ማዘጋጀት (ለበለጥ መረጃ፣ ***ሙያዊ እድገት*** ክፍል ይመልከቱ)፤
   - የትምህርት ቤት መዋቅሮች/ሥርዓቶች
   - ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ትምህርት
   - ለልዩ ጣልቃ-ገብ የትምህርት ድጋፍ የሚሰጥ ሚላሽ
   - የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት(መቅሰም)
   - የትምህርት ክትትል/የተማሪ ሥርዓት ፖሊሲ
   - የማርክ (ነጥብ) አሰጣጥ ፖሊሲ
   - 'Power school'/ፓወር ስኩል የሚባል የተማሪ አጠቃላይ መረጃ ማግኛ ድረ-ገጽ
   - የመማሪያ ክፍል ሥራ/የቤት ሥራ ፖሊሲዎች
   - ከተማሪና ከወላጅ የሚጠበቁ ነገሮች
   - የኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራምን መተነተን/ የቀለም ትምህርት ተለውጦ ሚዘናዎች/የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መገመገሚያ ነጥቦች
2. የትምህርት ቤት የቤተሰብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽሁፍና የምንባብ ትምህርት ፕሮግራሞችን መቀጠል።
3. ዘላቂ መተሳሰብ ያለበት ማኅበረሰብን መፍጠርና መደገፍ እንዴት እንደሚቻል ለሁሉም ሰራተኞች ሥልጠና መስጠት።
4. ለወላጆች በራሳቸው ቋንቋ በጽሁፍ ወይም በቃል መረጃዎችን መስጠት።
5. ሰራተኞች ወላጆችን በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ የሚያሳተፉባቸውን ዕድሎች መፍጠርና ማዘጋጀት።
6. በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ፣ የድስትሪክቱን ማኅበረሰብ ባህልና ቋንቋ የሚያውቅና የማኅበረሰቡ አባል የሆነን ሰውን መመልመልና መቅጠር።

## የወላጆች ተሳትፎ ሰንጠረዥ

| ምን | ድጋፎች |
|---|---|
| ወላጆችን መደገፍ – በትምህርት ቤት ሥርዓት መሰረት ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት የሚሳተፉባቸውን መንገዶች ማመቻቸትና በአስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች/ቁሳቁሶች መደገፍ። | በትምህርት ቤት የሥነ-አይምሮ ጤና ባለሙያዎች ለወልጆች የሚሰጥ ሥልጠና።<br>የወላጅ የቀለም ትምህርት<br>የወላጅ መምህር ኅብረት ስብሰባዎች<br>የወላጅ ውይይቶች<br>በትምህርታቸው ለተሳካላቸው ተማሪዎች መተባበር ስብሰባዎች |
| መገናኛ – የትምህርት ቤት ፕሮግራሞችንና ሥርዓቶችን ለወላጆች ማሳወቂያ መንገዶች፣ እንደዚሁም ለወላጆች ከትምህርት ቤት ጋር መገናኛ መንገዶች ናቸው። | የድስትሪክት የስልክ መልእክት ሥርዓት<br>የትምህርት ቤት ፓምፕሌቶች (በራሪ ጽሁፎች)<br>ቤት የሚላኩ ደብዳቤዎች/አስተርጓሚዎች<br>የአስተርጓሚዎች ስልክ ቁጥር/አድራሻ<br>ዜና መጽሄት/ትርጉም<br>ለወላጆች በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃዎችን የሚሰጡ ሰራተኞችን መመደብ<br>የወላጅ መመሪያ መጽሐፍ<br>ለወላጆች የስልክ ቁጥራቸውን በመጠቀም መረጃዎችን መስጠት<br>የወላጅ የመረጃ ምሽት |
| ትምህርት ቤትን መደገፍ – ወላጆች የትምህርት ቤት ተግባራትን/ዝግጅቶችንና በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚደግፉባቸው መንገዶች። | የነጻ አገልግሎት እድሎች<br>ገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች<br>ውይይቶች<br>ጉባዔዎች<br>የመስክ ጉብኝቶች |
| | |

| | |
|---|---|
| በቤት መማር – ወላጆች በቤት ልጆቻቸውን በትምህርታቸው እንዲረዱ እንዲቻል ትምህርት ቤት ለወላጆች የሚሰጥ የመማር እድሎች። | የቤት ሥራዎችን ትርጉም ወደ ቤት መላክ<br><br>የወላጅ የየቤት ሥራ ቡድኖች/ክለቦች<br><br>የወላጅ የሥርዓተ-ትምህርት ምሽት<br><br>የወላጅ የመረጃ መረብ<br><br>የወላጅ የመረጃ ምሽቶች<br><br>የመምህር/የወላጅ ቡድን የመማሪያ ክፍል ውስጥ ጊዜ<br><br>የወላጅ ውይይቶች |
| ውሳኔ መውሰድ – ወላጆች በትምህርት ቤት ውሳኔዎች ውስጥ የሚሳተፉባቸው መንገዶች/ረገዶች | የትምህርት ቤት ሥርዓቶች የወላጆች የዳሰሳ ጥናት<br><br>በትምህርታቸው ለተሳካላቸው ተማሪዎች የሚወሰዱ የጋራ ውሳኔዎች<br><br>የወላጅ መምህር ህብረትና ተጠያቂነት ኮሞቴዎች<br><br>የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት (መቅሰም)<br><br>የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪን መለየት/መከታተል/ማጠናቀቅ ውይይቶች |
| ከማህበረሰብ ጋር መተባበር-ወላጆና ትምህርት ቤት የማህበረሰብ ድርጅቶችን በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚያሳትፉባቸው መንገዶች። | የቤተሰብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽሁፍና ምንባብ ትምህርት ማዕከል<br><br>የትምህርት ቤትና የማህበረሰብ ሽርክና/ትብብሮች<br><br>የድስትሪክት በሞላ ውይይቶች<br><br>ቀስቃሽ/አነሳሽ ተናጋሪዎች<br><br>የመስክ ጉብኝቶች<br><br>የማህበረሰብ የባህል ማዕከላት |



*"ስብጥርነት በለለበት አመለካከት ነው ያደኩት።ለነ የሚመስለኝ ህይወት  አንድ ዓይነትና ሌሎች አመለካከቶች ያልተቀላቀሉበት ንጹህና መንገድ ነው።"*

***-ኤድዋርድ ጅምስ ኦልሞስ***

**ፈላሾችና ስደተኞች፤**

የቼሪ ክሪክ  ትምህርት ድስትሪክት ለፈላሾችና ለስደተኞች ቤተሰቦች የሚረዱ የተወሰኑ መርጃዎችና ድጋፎችን ለሰራተኞችና ለማኅበረሰብ አባላት ይሰጣል።  የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ከተለያዩ ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶች፣ የሠፈራ ድርጅቶችና ከሌሎች  ድርጅቶች ጋር ይሰራል፤



- Colorado Refugee Services Program (CRSP)
  (በኮሎራዶ የሚገኝ የስደተኞች አገልግሎቶች ፕሮግራም)
- African Community Center
  (የአፍሪካ ማኅበረሰብ ማዕከል)
- Ecumenical Refugee Services
  (እኩሜኒካል (ዓለም አቀፍ) የስደተኞች አገልግሎቶች)
- Jewish Family Service
  (ቤተ እሥራኤላዊ የቤተሰብ አገልግሎት)
- Lutheran Family Services
  (ሉተራን የቤተሰብ ስገልግሎቶች)
- The Learning Source
  (የትምህርት ምንጭ)
- Spring Institute for Intercultural Learning
  (ስፕሪንግ እንስቲቱት ሁለገብ ትምህርት ማዕከል)
- Rocky Mountain Survivor Center
  (ሮኪ ማውንተን የተራፊዎች/የቅሪቶች ማዕከል)

እነዚህ ድርጅቶች የቤት፣ የጤና እንክብካቤ፣ የአይምሮ ጤንነት አገልግሎቶች፣ የቅጥር በፊት ሥልጠናዎች፣ የምግብ አገልግሎቶችና ማረፊያ ቦታን መፈለግ፣ የህግ ድጋፎች፣ የቋንቋ ትርጉም/ፍች፣ የጎልማሳ ትምህርትና የጎልማሳ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ትምህርቶች ሊሰጡ ይችላሉ። የቼሪ ክሪክ ሰራተኞችና ቤተሰቦች በደንቨር ከተማ አካባቢ በኮሎራዶ ሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል ለስደተኞች የተለያዩ ድጋፎችን የሚሰጡ  የድርጅቶች ስም ዝርዝር አላቸው።

በተጨማሪም፣  የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የስደተኞች ጉዳይ በተመለከተ ለሰራተኞች ሥልጠና ይሰጣል።  ባለፉት ጊዜያት፣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ከስፕሪንግ እንስቲቱት ጋር በመተባበር አዲስ መጪ ስደተኞችንና  ለስደተኞቹ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች በተመለከተ ሁለገብ ሥልጠና ይሰጣል።  በተጨማሪም፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለስደተኞች ተማሪዎች የተሻለ ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ከአገር አቀፍ ትምህርት ድስትሪክቶች በመላ ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችን ይጠቀማል።

---

**አዲስ መጪዎች፤**

የተወሰኑ ትምህርት ቤቶች የአዲስ መጪ ተማሪዎች ፕሮግራም አላቸው። ይህ ፕሮግራም ተማሪዎቹ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪዎች ጋር ለተወሰኑ ሳምንታት የእንግሊዝኛ ቋንቋን በሰፊ የመርጃ መሳሪያዎች የሚማሩበትና ወደ መደበኛው መማሪያ ክፍል ሲሄዱ ቋንቋን በትምህርት ደረጃቸው የይዘት ትምህርት ውስጥ የሚማሩበት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።



**የቤተሰብ የመጻፍና ማንበብ ፕሮግራሞች፤**

የወላጆችን የትምህርት ቤት ተሳትፎ ለማሳደግ የጎልማሶች እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትና ለተማሪ ቤተሰቦች መጻፍና ማንበብ ትምህርት ለመስጠት የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለ***ጎልማሶችና ለቤተሰቦች የመማር ምንጭ*** *ጋር በመተባበር ይሰራል።*

የቤተሰብ የመጻና የማንበብ ፕሮግራሞች በሶስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሰጣሉ። እነዚህ አገልግሎቶች የሚሰጡት የቀጣይ ዜጎች በትምህርታቸው አለመሳካት፣ እንደዚሁም ወንጀልና ሁከትን የመፈጸም ጉዳይ መሰረቱ ወላጆች በመሆኑ ነው። የወላጆች መጻፍና ማንበብ ፕሮግራም ወላጆች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች መሆናቸውን በገንዘብ፣ ወላጆች እንደየባህላቸውና እንደየችሎታቸው ልጆቻቸውን በተሻለ መልኩ እንዲረዷቸው የአቅም ግንባታ ሥራን ይሰራሉ፤ እንደዚሁም አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህ ፕሮግራም ድንቁርናን ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለወላጆችና ለልጆች የጋራ ጊዜ በመስጠትና ለወላጆች የጎልማሶች መሰረተ-ትምህርትን፣ የልጆች ትምህርትን፣ የወላጅነት ክህሎት ሥልጠናዎችን ይሰጣል። በተጨማሪም፣ የተጨቆኑ ወላጆች የትምህርት ክንውኖችን ለማሻሻል ከህዝብ፣ ከግል፣ እንደዚሁም ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ ይህ ፕሮግራም የሥራ ላይ ሥልጠናን ይሰጣል።

*"ከሌሎች ጋር በደንብ ለመግባባት፣ ሁላችንም የተለያዩ የየራሳችን ግንዛቤዎች እንዳሉንና ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነቶች በግንዛቤዎቻችን ላይ እንደሚመሰረቱ ማወቅ አለብን..."*

*-አንቶኒ ሮብንስ*

የቋንቋ ተርጓሚዎችና ፈቺዎች ዓላማ

- የትምህርት ቤት መመለሻ ምሽቶች
- የወላጅ-መምህር ስብሰባዎች
- የቤት የስልክ ጥሪዎች
- የጤና ጉዳዮች፣ ክስተቶች፣ የስብሰባዎች ማስታወሻ፣ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች፣ የትምህርት ክትትልና የትምህርት ጉዳዮች
- የወላጆች የመረጃ ምሽቶች
- ልዩ ትኩረት የሚሻ ትምህርት የሰራተኞች ቅጥር
- ለጣልቃ መግባት ምላሽ መስጠት
- ለጊዜው ከመደበኛው ትምህርት ቤት በመታገድ የሚቀርብ የአቤቱታ ማቅረቢያ ችሎት
- ልዩ ሁነቶች
- በትምህርታቸው የተሳካላቸው ተማሪዎች ህብረት
- የወላጅ-መምህር ህብረት
- የጽሁፍና የቃል ትርጉም፤ ያም፣ በውጪ ቋንቋ የተጻፉት የክትባቶች መረጃ፣ በቃል ወደ እንግሊዝኛ ይተረጎማሉ።
- የትምህርት ቤት ወይም የድስትሪክት ሰነዶች



አስተርጓሚዎቻችን እነማን ናቸው ?

- የድስትሪክት የባህልና የቋንቋ ድጋፍ ሰጪዎች፤

| | |
|---|---|
| አረብኛ | ሩሲያኛ |
| አማርኛ | ስፓኒሽ |
| ፈረንሳይኛ | ትግሪኛ |
| ኮሪያኛ | ቬትናሚስ |
| ኦሮሞኛ | |

- የኮንትራት አስተርጓሚዎች
- ዲስትሪክት ያጸደቃቸው አስተርጓሚዎች(በዲስትሪክቱ እውቅና ሥር የሚያገለግሉ አስተርጓሚዎች)።

*"ውጤታማ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴን ተጠቀም/ሚ። ከዚያም የበለጠ ውጤታማ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ይመነጫል።"*

*- ፒተር ኤፍ ድራከር፣ የአሜሪካ ሊቅና ደራሲ*

**ዓላማ፤**

የድስትሪክት እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞች ግምገማ ሁለት ዓላማዎች አሉት። የግምገማ ትርጉም ስለ ፕሮግራም ውሳኔ መስጠት አስመልክቶ መረጃ ይሰጣል። ስለዚህ፣ የግምገማ ዋና ዓላማ፣ ውጤታማ የሆነ የፕሮራም ውሳኔ እንዲያደርጉ ለቼሪ ክሪክ ሰራተኞችና ትምህርት ቦርድ በቂ መረጃ ለመስጠት ነው። ከግምገማችን የሚናገኝ፤

- ድስትሪክት የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች፣ የሰራተኞች እውቀትና ብቃት፣ እንደዚሁም ወቅታዊ የፕሮግራም ልምምዶች
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ፍላጎት እያሟሉ የሰራተኞች ብቃትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለማወዳደር የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም መሻሻል፣
- ሠራተኞች የሚከተሉትና ሥራ ላይ የሚያውሉት ፕሮግራም እንደታቀደው መሆኑን መወሰን፣
- የፕሮግራማችንን ውጤታማነት መገምገም፤ ፕሮግራሙ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ምን ያህል ውጤታማ ነው?

ሁለተኛ ዓላማው የፌዴራል፣ የክፍለ ግዛትና የውስጥ የገንዘብ ድጎማዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ ድስትሪክቱ በሚያካሂደው ግምገማ ላይ በመሳተፍ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ነው። ይህንን ዓላማ በማንገብ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራምን የማያውቁ ሰዎች ሪፖርታችንን አንብበው የግምገማችንን ዓላማ፣ በግምገማው የተካተቱትን ጉዳዮች/ጥያቄዎች፣ መረጃዎቹን ለማሰባሰብ የሚረዱ ሂደቶችና እነዚህ መረጃዎች ስለፕሮግራማችን የሚገልጹት ጉዳይ ሊረዱ በሚችሉበት ሁኔታ እናቀርባለን።



(ዋቢ መጽሀፍ: Patton, M. Q. (1997). *Utilization-focused evaluation.* (3rd ed.) Thousand Oaks, CA: Sage.1997).

## ግምገማ

## የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

በኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራም ላይ በመመሰረት፤

- የኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራም ላይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቂ እድገት እያሳዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አማካይ የእድገት ፐርሰንታይሎቻቸውን መቆጣጠር። ይህም የሚሆነው እንደሚከተለው ነው፤
  በትምህርት ቤት በክፍል ደረጃቸው በድስትሪክት
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በትምህርት ይዘቶች ዙሪያ የብቃት ደረጃቸው የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተወላጅ ተማሪዎችንና በቅርብ ጊዜ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ትምህርት ፕሮግራም የተላቀቁና እንግሊዝኛ የተወላጅ ቋንቋቸው ያልሆነ ተማሪዎች የቋንቋ የብቃት ደረጃ በኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራምና በሌሎች መደበኛ መገምገሚያ ፈተናዎች ማጣራት፤
  በትምህርት ቤት በክፍል ደረጃቸው በድስትሪክት
- የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አማካይ የእድገት ፐርሰንታይል ከሌሎች ተመሳሳይ ድስትሪክቶች ጋር ማወዳደር(የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፐርሰንተጅ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ደረጃ፣ ወዘተ)።

---

**የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መገምገሚያ ላይ በመሞርኮዝ፤**

- ድስትሪክቱ በክፍለ-ግዛት የተወሰኑትን ዓመታዊ ሊለካ የሚችል የክንውን ግቦች #1 እና #2 (#1- ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ትምህርት እድገት፣ እና #2-የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ደረጃ ላይ መድረስ)።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገትና ብቃትን በተመለከተ ዓመታዊ ሊለካ የሚችል የክንውን ግቦች መረጃን ከተመሳሳይ ድስትሪክቶች ጋር ማወዳደር።
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገትና ብቃትን በተመለከተ ዓመታዊ ሊለካ የሚችል የክንውን ግቦች መረጃን በድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ማወዳደር።

---

**ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎች**

- የወላጅና የተማሪ የትኩረት ቡድኖች
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለሙያ ዳሰሳ
- የመማሪያ ክፍል አስተማሪ ዳሰሳ
- የአስተዳደር ዳሰሳ

---

**ውጤቶች**

- ለኃላፊዎቹና ለትምህርት ቦርዱ ተልከዋል
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተወላጅ ተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፕሮግርምን ለማሻሻልና አስፈላጊውን ለውጦች ለማድረግ ይጠቅማል።

# የቃላትና የምህፃረ-ቃላት ማውጫ

| ምህፃረ-ቃላት | ቃላት | ትርጉም/ገለጻ |
|---|---|---|
| AMAO | ዓመታዊ ግልጽ የሆነ የክንውን ግቦች | 'Title III' በሚባል የፌዴራል መንግሥት ፕሮግራም የሚደጎም ሆኖ የቋንቋ ትምህርት ውጤታማነትን ለመገምገም የሚረዳ የተጠያቂነት ሥርዓት ነው። |
| AYP | በቂ ዓመታዊ መሻሻል | በተማሪ የፈተና ተሳትፎ፣ ምረቃ፣ የትምህርት ክትትልና በሒሳብና በምንባብ ትምህርቶች ክንውን ላይ በመሞርኮዝ የተማሪን ተለውጦ ለመወሰን የሚረዳ ዓመታዊ ግልጽ የሆነ መስፈርት። |
| BOE | መረጃ | ተማሪን ለመቆጣጠርና እንደገና ለመመደብ የሚረዱ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች። |
| CELA | የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መገምገሚያ | በክፍለ ግዛት የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎች ላይ በመመስረት፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተማሪዎች የንግግር፣ የመስማት፣ የምንባብና የጽሁፍ ብቃቶች መገምገሚያ። |
| | የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መገምገሚያ የብቃት ደረጃዎች | የእያንዳንዱ የቋንቋ የክህሎት የብቃት ደረጃዎች፤ መስማት፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ናቸው። ደረጃዎቹ ጀማሪ (1)፣ ጀማሪ መሃከለኛ (2)፣ መሃከለኛ (3)፣ ብቁ (4)፣ ከብቁ በላይ (5) ያካትታሉ። |
| | ድልደላ | የትምህርት ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚረዳ የተማሪዎች የድልደላ ስልት። |
| | አብሮ ማስተማር | ሁለት ወይም ከዚያም በላይ አስተማሪዎች የተወሰኑ ወይም ሁሉንም የክፍል ተማሪዎች የማስተማር ኃላፊነት ይጋራሉ። ለተማሪዎች ትምህርት በጋራ ለማቀድ፣ በጋራ ለማስተማርና በጋራ ለመገምገም የጋራ ኃላፊነት እንዲኖራቸውም እድል ይሰጣል። |
| CRI | ባህልን መሰረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሂደት | መማርን ለተማሪዎች ተገቢና ውጤታማ ለማድረግ፤ ባህላዊ እውቀት፣ የቀድሞ ልምድና የተለያዩ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ዘይቤ የሚጠቀም የማስተማር ቀረቤታ ይጠቀማል፤ የሁሉንም ተማሪዎች ጠንካራ ጎን በመጠቀም ያስተምራል። እንደ ውርስ ሆኖ የተማሪዎችን መገኘት፣ አመለካከቶችና የትምህርት አቃባበል ዘይቤዎችን የሚወስንና በመደበኛው ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡ ለተለያዩ ጎሳዎች ባህላዊ ቅርስ ህጋዊነት እውቅናን ይሰጣል(Gay, 2000)። |
| CSAP | በኮሎራዶ የተማሪ መገምገሚያ ፕሮግራም | በክፍለ-ግዛት በሞላ የሚሰጥ ግምገማ "... የተዘጋጀው በኮሎራዶ ክፍለ-ግዛት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት መደበኛ መመዘኛዎችን ለማሟላት ያላቸውን የትምህርት ተለውጦና በዚህ ረገድ ትምህርት ቤቶች ምን እየሰሩ እንደሆኑ ለመረዳት እንዲቻል ነው (የኮሎራዶ ትምህርት ቢሮ ድረ-ገጽ፣ 2009)። |

# የቃላትና የምህፃረ-ቃላት ማውጫ

| ምህፃረ-ቃላት | ቃላት | ትርጉም |
|---|---|---|
| DIBELS | የመሰረታዊ የመጻፍና የማንበብ ክህሎቶች ንቁ አመላካቶች | ሥርዓተ-ትምህርትን መሰረት ያደረገ ሚዛና የወጣት ተማሪዎችን የምንባብ ፍሎታዎች መሻሻልን ለመከታተል ይረዳል። |
| DRA2 | የምንባብ መሻሻል/እድገት ግምገማ | ሥርዓት ባለው ምልከታ/አስተውሎት፣ በቀረጻና በክንውን ግምገማ የተማሪዎችን የምንባብ ክንውን ለመለየት የሚረዳ የምንባብ ግምገማ ነው። በመጀመሪያ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሥራ ላይ ይውላል። (DRA2 ድረ-ገጽ፣ 2009) |
| ELA | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት | ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተጨማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ድጋፍ ይሰጣል። ዓላማውም ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋና በትምህርታቸው ብቁ እንዲሆኑ ነው። |
| ELD | የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት/መሻሻል | ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ እድገት መመሪያዎች። የኮሎራዶ ክፍለ ግዛት ድስትሪክቶች፣ ትምህርት ቤቶችና አስተማሪዎች ተገቢውን የትምህርት ፕሮግራሞች ሲያዘጋጁ የሚመሩበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛዎች አሏቸው። |
| ELL | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ | እንግሊዝኛን እንደሌላ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች። |
| | ልዩ ትኩረት የሚሹ ተማሪዎች | ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች፣ ስንኩላን ተማሪዎችና፣ ልዩ የትምህርት ትኩረት የሚሹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ተማሪዎች ናቸው(የኮሎራዶ ትምህርት ቢሮ)። |
| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም ፕሮግራም ያጠናቀቁ ተማሪዎች | እንግሊዝኛን አቀላጥፈው የሚናገሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችና ከሁለት ዓመት ክትትል በኃላ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅሰም አገልግሎት የማያስፈልጋቸው ተማሪዎች። |
| | ማሰስ/መመርመር | ሥርዓተ ትምህርትን መሰረት ካደረጉ ሦስት የፈተናዎች ፕሮግራሞች ውስጥ የመጀመሪያው የኮሌጅ ዝግጁነት ሥርዓትን ያካትታል። ፕሮግራሙ የተዘጋጀው የ8ኛና የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የኮሌጅ ዝግጁነትን እንዲረዱ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውና ከዚያም በኃላ ላለው አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉና የወደፊት የትምህርትና የሥራ ሁኔታቸውን ሲያቅዱ እንዲረዳቸው ነው። |

| ምህፃረ-ቃላት | ቃላት | ትርጉም |
|---|---|---|
| FEP | ቆልጣፋ | በተለያዩ አውዶች ውስጥ ስለተለያዩ ማህበራዊና ትምህርታዊ ሪዕሶችን በተመለከተ የተለመዱና አዳዲስ ጉዳዮችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መረዳትና መግባባት የሚችሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች። የትምህርት ይዘትን በተመለከተ ከተወላጅ የእንግሊዚዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ተመሳሳይ ክንውን ያላቸው፣ ነገር ግን ውስን የሥነ ቋንቋ ወይም የሥነ ልሳን ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎች። |
| GT | ልዩ ተሰጥኦ ያለው/ያላት | ምሁራዊ፣ የፈጠራ፣ ጥበባዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ወይም በተወሰኑ የትምህርት ዙሪያዎች ከፍተኛ ችሎታ እንዳላቸው ያረጋገጡ ተማሪዎች። |
| HLS | የቤት ቋንቋ ዳሰሳ | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመመልመልና ተገቢውን የትምህርት እድሎች ለመስጠት እንዲረዳ በምዝገባ ጊዜ የተሞላ ፎርም። |
| IEP | ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም | በየአካለ ስንኩላን ግለሰቦች አዋጅ መሰረት የተዘጋጀና በስብሰባ ውስጥ የተከለሰ የእያንዳንዱ ተማሪ የጽሁፍ መግለጫ |
| | የ 'Lau' ሕግ | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የብቃት ደረጃን ለመመዘገብ የሚረዱና ህጎችን የሚፈልጉ (የ 'Lau' ህጎች የሚባሉ) የ 1974 የ 'Lau እና Nichols' ህጋዊ ጉዳዮችን ይመለከታል። |
| LEP | ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት | አብዛኛዎቹን የማህበራዊ ጉዳዮች ሊረዱና ሊያስረዱ የሚችሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ይመለከታል። አእምሮን ለሚፈልጉ የትምህርት ይዘቶች ዙሪያ ብቃት እያገኙ ሊሄዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን፣ ያለ ሥነ ቋንቋ(ሥነ ልሳን) ድጋፍ በየትምህርት ዙሪያዎች በሙላት ለመሳተፍ ዝግጁ ዝግጁ አይደሉም። |
| MAP | የትምህርት እድገት ሚዘና | የክፍለ ግዛት ሥርዓተ-ትምህርትን ያቀፈና በኮምፒዩተር የታገዘ፣ እንደዚሁም የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት መረዳት ደረጃና የትምህርት እድገትን በየጊዜው የሚመዝን የጠቅላላ እውቀት መመዘኛ ፈተና ('NWEA MAP' የሚባል ድረ-ገጽ 2009)። |
| | ክትትል 1፣ ክትትል 2 | በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደ ቆልጣፋ እንደገና የተመደቡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ስኬታማነታቸውን ለመወሰን ለሁለት ዓመታት ክትትል ይደረግላቸዋል። (የኮሎራዶ ትምህርት ቢሮ) |
| NCLB | አንድ(ት)ም ተማሪ በትምህርቱ/ቷ ወደ ኃላ እንዳይቀር/እንዳትቀር | የ2001 አንድ(ት)ም ተማሪ በትምህርቱ/ቷ ወደ ኃላ እንዳይ(ት)ቀር የሚመለከት አዋጅ ('NCLB' የሚባል የእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃል) የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አዋጅ ('ESEA' የሚባል የእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃል) እንደገና አጸደቀ-- ከመዋዕለ ህጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ዋነኛ የፌዴራል ህግ። አንዲ(ት)ም ተማሪ በትምህርቱ(ቷ) ወደ ኃላ እንዳይ(ት)ቀር የሚል አዋጅ በአራት ህግጋት ላይ ይመሰረታል፤ ለውጤቶች ተጠያቂነት መውሰድ፣ ለወላጆች ተጨማሪ አማራጮችን መስጠት፣ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ እንደዚሁም በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ላይ በመሞርኮዝ ሊተገበሩ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮር። |

| ምህፃረ-ቃላት | ቃላት | ትርጉም |
|---|---|---|
| NEP | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት የለለው/የለላት ተማሪ | የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ውስብስብ ያልሆኑና የተለመዱ መግባቢያ ቋንቋዎችን መረዳትና ምላሽ መስጠት የጀመሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች። |
| | አዲስ ገቢ | የተወሰነ ወይም ምንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት የለላቸውና በአገራቸውም በቋንቋቸው የተወሰነ መደበኛ ትምህርት ሊኖራቸው የሚችሉ የቅርብ ጊዜ ፈላሾች (የ 2009 'Center for Applied Linguistics website' የሚባል ድረ-ገጽ)። |
| NNAT | 'Naglieri' የሚባል ንግግራዊ ያልሆነ የችሎታ ሚዛና | ንግግራዊ ያልሆኑ ጠቅላላ ችሎታዎች። እነዚህ ቴስቶች የተለያዩ ባህልና ቋንቋ ላላቸው፣ እንደዚሁም የመስማት ችግር ላለባቸው ወይም መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ፍትሃዊ የችሎታ ግምገማ ትልቅ ጥቅም አለው። ይህም ምክንያቱ ጥያቄዎቹ ማንበብ፣ መጻፍ፣ ወይም መናገር አይፈልጉም።('http://en.wikipedia.org/wiki/NNAT' ድረ-ገጽ)። |
| OCR | የዜጎች መብቶች ቢሮ | የዜጎች መብቶች ጥሰቶችን የሚቆጣጠር የፌዴራል መንግሥት ክፍል። የትምህርት ድስትሪክቶች የጎሳ ወይም የቋንቋ መድልኦ ጥሰትን በተመለከተ ወላጆችና አስተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ ለክፍሉ ሊሰጡ ይችላሉ። |
| PALS | የሥነ ድምጽ እውቀት የመጻፍና የማንበብ ችሎታ መመዘኛዎች | ከመዋእለ ሕጻናት እስከ 3ኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች መሰረታዊ የማንበብና የመጻፍ ችሎታዎችን መገምገሚያ ፈተና። |
| | እቅድ | 'ACT' የሚባል ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለኮሌጅ ዝግጁ መሆንን ለመገምገም የሚሰጥ ፈተና። የተማሪዎችን ወቅታዊ የትምህርት እድገት የሚመዝን፣ የሥራ/የሥልጠና አማራጮችን መመርመር/ማሰስ፣ እንደዚሁም ለቀሩት የሁለተኛ ደረጃና ከዚያም በኃላ ላሉት የትምህርት ዓመታት እቅዶችን መዘርጋት ('www.act.org/plan/' ድረ-ገጽ)። |
| RtI | የጣልቃ መግባት ምላሽ | ተማሪዎች በጠቅላላ ሥርዓተ-ትምህርት በቂ መሻሻል ሳያሳዩ ሲቀሩ ጣልቃ ገብቶ የመርዳት ሞዴል (አብነት)፣ እንደዚሁም ተማሪዎች ለጣልቃ-ገብ ድጋፉ የሚሰጡትን ምላሽ መገምገም። በተጨማሪም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችንና ሌሎች የትምህርት ችግር/ስንኩልነት ያለባቸው ተማሪዎችን ልዩ ትኩረት በሚሻ ትምህርት ውስጥ መመደብ። |
| | በቋንቋ ትምህርት የታገዘ የይዘት ትምህርት አሰጣጥ | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ብቃታቸውን እያሳደጉ የክፍል ደረጃቸውን የትምህርት ይዘት ግልጽ ለማድረግ የተዘጋጀ የትምህርት ዓይነት። አስተማሪው/ዋ የተለያዩ ዘዴዎችንና ስልቶችን በመጠቀም ቋንቋንና የትምህርት ይዘትን በማቀናጀት ትምህርቱን ከማህበራዊና ከባህላዊ እውቀቶች ጋር ያዋህዳሉ። |
| | በቋንቋ ትምህርት የታገዘ የትምህርት አሰጣጥ | ቋንቋንና ይዘትን በማዋሃድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የማስተማር ዘዴ። የዚህ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ግቦች ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው መደበኛውን የትምህርት ይዘት እያገኙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት እንዲያጎለብቱ ነው። |

# ተጨማሪ መረጃዎች

# ተጨማሪ መረጃ ሀ– የቤት ቋንቋ ዳሰሳ

**ቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት #5 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መረጃ**

ሐምሌ 1981 የተላለፈው የኮሎራዶ ረቂቅ አዋጅ 462 – የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት አዋጅ (22-24-101 CRS)፣ ፣ እና በ 1974 የወጣው የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ'Lau' ውሳኔ፣ በህዝብ ትምህርት ቤት የተመዘገቡትን የተማሪዎች ቆጠራ እንዲካሄድ ይፈልጋል። የቆጠራው ዓላማ የተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ለመወሰን ነው።

| የአያት ስም | የተማሪ ስም | እድሜ | የትውልድ ዘመን | የክፍል ደረጃ | ጾታ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ወንድ | ሴት |

የወላጅ/የአሳዳጊ ስም፡ ______________________________ ቀን ______________

አድራሻ ______________________________________ የስልክ ቁጥር ______________

የወላጅ ኢ-ሜል (ካለ) ______________________________________

የተማሪ የትውልድ አገር ______________________ አሜሪካ የገባበት/የገባችበት ቀን______________

1. **የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት የሚያመላክት ምድብ ይምረጡ፤**

☐ ምድብ ሀ **እንግሊዝኛን ሳይሆን ሌላ ቋንቋ ብቻ** ይረዳል/ትረዳለች፣ ይናገራል/ትናገራለች፣ ያነባል/ታነባለች እና/ወይም ይጽፋል/ትጽፋለች።

☐ ምድብ ለ **ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ይልቅ ሌላ ቋንቋን** የበለጠ ይረዳል/ትረዳለች፣ ይናገራል/ትናገራለች፣ ያነባል/ታነባለች እና/ወይም ይጽፋል/ትጽፋለች።

☐ ምድብ ሐ **እንግሊዝኛንና ሌላ ቋንቋን በእኩልነት** ይረዳል/ትረዳለች፣ ይናገራል/ትናገራለች፣ ያነባል/ታነባለች እና/ወይም ይጽፋል/ትጽፋለች።

☐ ምድብ መ **ከሌላ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛን** የበለጠ ይረዳል/ትረዳለች፣ ይናገራል/ትናገራለች፣ ያነባል/ታነባለች እና/ወይም ይጽፋል/ትጽፋለች።

☐ ምድብ ሠ ሌላ ቋንቋን ሳይሆን **እንግሊዝኛን ብቻ** ይረዳል/ትረዳለች፣ ይናገራል/ትናገራለች፣ ያነባል/ታነባለች እና/ወይም ይጽፋል/ትጽፋለች።

2. **በቤት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ ካለ፣ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኛው (የትኞቹ) ቋንቋ (ዎች) እንደሆነ (ኑ) ያመላክቱ፤**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ☐Arabic (አረብኛ) | ☐Amharic (አማርኛ) | ☐Cambodian (ካምቦዲያ) | ☐Cantonese (ካንቶኒኛ) | ☐Farsi (ፋርሲ) |
| ☐Hindi (ህንዲ) | ☐Korean (ኮሪያ) | ☐Mandarin (ማንዳሪን) | ☐ Oromo (ኦሮሞ) | ☐Persian (ፐርሺያ) |
| ☐Portuguese (ፖርቱግኛ) | ☐Russian (ሩሲያ) | ☐Somali (ሶማሊኛ) | ☐Spanish (ስፓኒሽ) | ☐Thai (ዛይ) |
| ☐Tagalog (ታጋሎግ) | ☐Urdu (ኡርዱ) | ☐Vietnamese (ቬተናም) | ☐Other Language(s): ______________ | |

3. **ከላይ የተጠቀሰው ቋንቋ (ከእንግሊዝኛ ውጪ) ምን ያህል በቤት ውስጥ ይነገራል?**

☐ሁል ጊዜ ☐ብዙ ጊዜ ☐አንዳንዴ ☐እምብዛም

4. **ተማሪው/ዋ ስፓኒሽ ነው/ናት / የላትኖ ወይም ከስፓኒሽ ስረ ነገር ነው/ናት? አዎን ☐ አይ ☐**

*ከኩባ፣ ከመክሰኮ፣ ከፑርቶ ሪኮ፣ ከደቡብ/መካከለኛ አሜሪካ ወይም ሌሎች ስረ ነገር ያለበት ሰው፣ የዘር ጉዳይ እንዳለ ሆኖ።*

5. **ለዚህ ተማሪ፣ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ጎራዎች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያም በላይ ይምረጡ፤**

☐ **ሰሜን፣ መሃከለኛ ወይም ደቡብ አሜሪካን እንዲያን ወይም የአላስካ ተወላጅ የሆነ፤** *ከቀድሞ የሰሜን አሜሪካ፣ የመካከለኛ ወይም የደቡብ አሜሪካ ሰዎች ጋር ዝምድና ያለው/ያላት ግለሰብ።*

☐ **ኤሺያዊ፤** *ከሩቅ ምስራቅ፣ ከደቡብ ምስራቅ ኤሺያ፣ ወይም ከእንዲያ ክፍለ አህጉር ሰዎች ጋር ዝምድና ያለው/ያላት ግለሰብ።*

☐ **ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ፤** *ከማንኛውም ጥቁር የአፍሪካ ጎሳዎች ጋር ዝምድና ያለው/ያላት ግለሰብ።*

☐ **ተወላጅ የሃዋይ ወይም ሌሎች የፓሲፍክ ደሴቶች ፤** *ከቀድሞ የሃዋይ ወይም ሌሎች የፓሲፍክ ደሴቶች ሰዎች ጋር ዝምድና ያለው/ያላት ግለሰብ።*

☐ **ነጭ፤** *ከቀድሞ የአውሮፓ፣ የሩቅ ምሥራቅ፣ ወይም የሰሜን አሜሪካ ሰዎች ጋር ዝምድና ያለው/ያላት ግለሰብ።*

6. **የልጅዎ የአፍ መከፈቻ ቋንቋ ምንድነው?** ______________________

7. **ልጅዎ፤**

ሀ. በሌላ የኮሎራዶ ትምህርት ቤት ተከታትሏል/ተከታትላለች? **አዎን** ☐ **አይ** ☐

አዎን ከሆነ፤ ድስትሪክት ____________________ትምህርት ቤት ____________________ለምን ያህል?_______

የትምህርት ቋንቋ ምን ነበር?______________________________________

ለ. ከኮሎራዶ ውጪ በአሜሪካ ውስጥ ላለፉት 12 ወራት ትምህርት ተከታትሏል/ተከታትላለች? **አዎን** ☐ **አይ** ☐

ሐ. ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሌላ አገር ትምህርት ተከታትሏል/ተከታትላለች? **አዎን** ☐ **አይ** ☐

መ. የእንግሊዝኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተከታትሏል/ተከታትላለች? **አዎን** ☐ **አይ** ☐

8. **ወደ ኮሎራዶ የመጡት ለእርሻ፣ ለግብርና ወይም ለአሣ ማስገር ሥራዎች ዓላማ ነው?**

**አዎን** ☐ **አይ** ☐

9. **በአሁኑ ጊዜ የእርሻ፣ የግብርና፣ ወይም የአሣ ማስገር ሥራዎችን እየሰሩ ነው?**

**አዎን** ☐ **አይ** ☐

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መረጃ

**ተማሪዎች በሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ዙሪያዎች ብቃት እስከኖራቸው ድረስ የእንግልዝኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎቶችን ያገኛሉ።**

Summative Assessment (OF learning)

Formative Assessment (FOR learning)

### መናገር

- ☐ CELA(የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ የመገምገሚያ ፈተና)
- ☐ ELD (የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መደበኛ መመዘኛዎች)
- ☐ ቢያንስ አንዱን ይምረጡ፤
  - ☐ የሥዕል መጽሀፍ የቋንቋ ናሙና
  - ☐ የቃል ታሪክን መልሶ መንገር
  - ☐ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቃለምልልስና መመሪያ
  - ☐ የሀሳብ ብቃት ፈተና (የቃል)
  - ☐ የአስተማሪ ምልከታ/መመዘኛ

### ማዳመጥ

- ☐ CELA (የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መመዘኛ ፈተና)
- ☐ ELD (የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መደበኛ መመዘኛዎች)
- ☐ ቢያንስ አንዱን ይምረጡ፤
  - ☐ የቃል ታሪክን መልሶ መንገር
  - ☐ መመሪያዎችን መከተል
  - ☐ የሀሳብ ብቃት ፈተና (የቃል)
  - ☐ የአስተማሪ ምልከታ/መመዘኛ

### ማንበብ

- ☐ CELA (የኮሎራዶ እንግሊዝኛ ቋንቋ መመዘኛ ፈተና)
- ☐ CSAP (የኮሎራዶ ተማሪዎች መገምገሚያ ፕሮግራም)
- ☐ PALS or DIBELS (ካለ)-የሥነ ድምጻዊ መጻፍና ማንበብ እውቀት መመዘኛ (የመዋዕለ-ሕጻናት-3ኛ ክፍል ሥርዓተ-ትምህርትን መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የመጻፍና የማንበብ ችሎታ መመዘኛ)
- ☐ DRA2 (ታዳጊ የምንባብ ችሎታ 2)
- ☐ ካርታ (አንደኛና መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)
- ☐ ምርምር (8ኛ ክፍል)
- ☐ እቅድ (10ኛ ክፍል)
- ☐ 'ACT' የሚባል የኮሌጅ መግቢያ ፈተና (ሁለተኛ ደረጃ)
- ☐ ELD -የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መደበኛ መመዘኛዎች
- ☐ ቢያንስ አንድ ይምረጡ፤
  - ☐ የሥነ ጽሁፍ ጽንሰ ሃሳቦች
  - ☐ ተከታታይ ሰነዶች (IRI)
  - ☐ የአስተማሪ ምልከታ መመሪያ
  - ☐ 'Houghton Mifflin' የሚባሉ መመዘኛዎች
  - ☐ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ደስትሪክት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ
  - ☐ የሃሳብ ብቁነት ፈተና (ምንባብ)

### መጻፍ

- ☐ CELA (የኮሎራዶ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መመዘኛ ፈተና)
- ☐ CSAP (የኮሎራዶ ተማሪዎች መመዘኛ ፕሮግራም)
- ☐ አሳማኝ፣ መዘርዝራዊና/ወይም ገላጭ ጽሁፍ ሙከራዎች
- ☐ PLAN (ሁለተኛ ደረጃ)
- ☐ የሁለተኛ ደረጃ ጽሁፍ መመዘኛ (11ኛ ክፍል)
- ☐ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መደበኛ መመዘኛዎች
- ☐ አንዱን ይምረጡ፤
  - ☐ አንድን ጉዳይ በጽሁፍ እንደገና መግለጽ
  - ☐ ባለ 6 መመሪያ
  - ☐ ገላጭ አንቀጽ
  - ☐ የአስተማሪ ምልከታ መመሪያ
  - ☐ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ
  - ☐ የሃሳብ ብቁነት መመዘኛ (ምንባብ)

### ሌላ

- ☐ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ጠቅላላ መመዘኛ
- ☐ የአስተማሪ/የቡድን ድጋፍ
- ☐ የወላጅ የቃል ዳሰሳ
- ☐ 'NNAT' የሚባል ቃላዊ ያልሆነ ችሎታ መመዘኛ ፈተና (አንደኛ ደረጃ)
- ☐ ከመደበኛ መመዘኛዎች የትምህርት እድገት ሪፖርት የሚገኙ ትንተናዎች (አንደኛ ደረጃ)
- ☐ በትምህርት ይዘት ዙሪያ የሚሰጡ የኮርሶች ውጤት
- ☐ የትምህርት ይዘት መመዘኛዎች፤
  - ☐ የኮሎራዶ ተማሪዎች መመዘኛ ፕሮግራም-ሳይንስ
  - ☐ የኮሎራዶ ተማሪዎች መመዘኛ ፕሮግራም-ሒሳብ
  - ☐ ካርታ- ሒሳብ
  - ☐ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰጡ መመዘኛዎች
  - ☐ ሥርዓተ-ትምህርትን መሰረት ያደረጉ መመዘኛዎች
  - ☐ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት ክንውን መመዘኛዎች
  - ☐ የምደባ የሒሳብ ፈተና
  - ☐ እቅድ – ሒሳብ
  - ☐ ምርምር- ሒሳብ